ብሏልና፤ ስለዚህ፡ነው።(ትሬት) ከግዜር፡ወዲያ፡ፈጣሪ÷ከባለ ቤት፡ወዲያ፡መስካሪ።ዓም፡ማለትም÷ያለፈውን፡ዘመን÷ወደ ም፡ከዘመን፡በሬት፡የኾነውን፡ወልድየ፡አንተን፡አያሳይም፤ሰው፡ ኹኖ፡ተቀብቶ፡ያለበትን÷የተቀባበትን፡ጊዜ፡እንጂ፡ማለት፡ነው።

የግዜር፡መንግሥት፡የሚባለውም፡ሉተራዊ፡ታሪክ፡በ፬፻ ፶፩፡ገጽ÷ዓ.ም፡ወአድኩከን፡ከወልድየ፡አንተ፡ለይቶ፡ስለ፡ባሕርይና፡ስለ፡ግብር፡ልዩት፡እንዲህ፡ይላል።በዚህ፡ዘመን፡ክርክር፡ተነሣ፡በስጳንያ÷ስለ፡ክርስቶስ፡መለኮትነት።፫፡መምህራን፡ነበሩ፡በስጳንያ÷የቶሌዶ፡ሜትሮፖሊታን፡ኤሊጳንዱስ፡የተባሉ፤ የውርጌልስ፡ኤጲስቆጶስም፡ፌሊክስ፡የሚሉት÷እንዲህ፡አስተማሩ።የሱስ፡ክርስቶስ፡በሰውነቱ፡የግዜር፡ልጅ፡እንዲኾን፡በመቀበል፡ነው፤ በመወለድ፡አይደለም፡በመለኮቱ፡ግን፡የግዜር፡ልጅ፡ነው፤ በዘላለም፡መወለዱ፡ከአብ፡ባሕሪ። እንዲህም፡ክርስቶስ፡በመለኮቱ፡የግዜር፡የባሕርይ፡ልጅ፡ኹኖ፡በሰውነቱ፡የጸጋ፡ልጅ።

በመጨረሻው፡ግን፡((ከዳዊት፡ትንቢት፡ከጳውሎስ፡ስብከት÷ከአፈ፡ወርቅና፡ከቄርሎስ፡ትምርት፡ከምሥራቃውያን፡ትርጓሜና፡አፈታት፡የተስማማች፡ይህች))፡የነፌልክስ፡ትምርት፡ተወግዘች፡ይላል። ግዝትና፡ርግማን፡አይገባበት፡የለም፤ ይልቁንም፡በሀገራችን፤ ንስጥሮስም፡ከጉባኤ፡በሬት፡ቄርሎስን፡እንደወገዘው፡በቤት፡ክሲያን፡ታሪክ፡ተጽፏል፡(ኢሳ፳፡፩)።

ጥያቄ፤የግብርና፡የጸጋ፡ልዩት፡ከወላዲና፡ከሠያሚ፡ከጸጋዊ፡ጋራ፡ያስተካክላልን።

ምላሽ፤ከግብርና፡ከጸጋ፡ወንድሞች፡ከተወራረሾች፡ቢያስተካክል፡እንጂ፤ከወላጁና፡ከሿሚው፡ካውራሹ፡አያስተካክልም።ይኸውም፡ሶበስ፡ታፈቅሩኒ፡እምተፈሣሕክሙ፡በሐዊሮትየ፡ኀበ፡አብ፤ እስመ፡ውእቱ፡አብ፡የዐብየኒ፡ባለው፡ይታወቃል፡(ሮሜ፡፰፡፲፬–፲፯። ዮሐ፲፬፡፳፰። ፩፡፲፯)። ወረሰየነ፡ዕሩያነ፡ምስሌሁ፡

www.ethiopianorthodox.org

፻፹፪

ብነ፡ሠለስቱ፡ልደታት፤ አሐቲ፡ጥምቀት፡ቅድስት፡እንተ፡ትሬስየነ፡ አምሳለ፡ክርስቶስ፤ ወአሐዱ፡ሥጋሁ፡ወደሙ፡ለክርስቶስ፡ዘይሰሪ፡ አበሳ፡ወኃጢአተ፤ ወአሐዱ፡አንብዕ፡ዘበንስሓ፡ዘይወፅእ፡እምውሳጥ፡በአምሳለ፡ዮርዳኖስ፡ወያቄርብ፡ንጹሐ፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡ እንዳለ(ቅዱ፡አት)። በጥምቀት፡የሚገኝ፡ልጅነት፡በኃጢአት፡ሲያረጅ፡ መታደሻው፡ንስሓና፡ቍርባን፡ስለ፡ኾኑ፥ጥምቀትን፡መደብ፡አድርጎ፡ ኹለቱንም፡ልደት፡አላቸው።

## ፫ኛ፡ ክፍል።

## ምስጢረ፡ቍርባን።

ጥያቄ፤ ቍርባን፡ማለት፥ ምን፡ማለት፡ነው። ምስጢረ፡ቍርባንስ፡እንደ፡ምን፡ ነው።

ምላሽ፤ ቍርባን፡ማለት፥ሰው፡በፈቃዱ፥ለግዚር፡የሚያቀርበው፤ሰውን፡ ወደግዚር፥እግዚርን፡ወደ፡ሰው፡የሚያቀርብ፡መንፈሳዊ፡አምኃ፥ መሥዕተ፡ሰላም፡ማለት፡ነው። የቍርባንም፡ሥርዐት፡እንዲህ፡ነው። ጌታ፡በምሴተ፡ኀሙስ፡ለራት፡ካመጡለት፡ኅብስትና፡ወይን፡በእጁ፡ ይዞ፡ወዳባቱ፡በጸለየ፡ጊዜ፥ኅብስቱን፡ወደ፡ሥጋው፥ወይኑን፡ወደ፡ ደሙ፡ለውጦ፥ስለናንተ፡ነገ፡የሚሠዋ፡ሥጋዬ፡የሚፈስ፡ደሜ፡ይህ፡ ነው፤ እናንተም፡እስከ፡ምጽአት፡ድረስ፡እንዲሁ፡አድርጉ፡ብሎ፡ ሰጣቸው። ዛሬም፡ቄስ፡ጌታ፡በምሴተ፡ኀሙስ፡እንዳደረገው፡ጸሎት፡ቅዳሴ፡በጸለየበት፡ጊዜ፥የጌታን፡ቃል፡ጠቅሶ፥ዝ፡ኅብስት፡ሥጋየ፡ውእቱ፡ሲል፥ኅብስቱ፡የኅብስትነቱን፡መልክ፡ሳይለቅ፡የክርስቶስ፡ሥጋ፡ወደ፡መኾን፡ይለወጣል። ወይኑም፡ዝ፡ጽዋዕ፡ደምየ፡ውእቱ፡ ሲል፥የወይንነቱን፡መልክ፡ሳይለቅ፡የክርስቶስ፡ደም፡ወደ፡መኾን፡ይለወጣል።

ጥያቄ፤ ቍርባን፡ምን፡ያደርጋል። ለመቍረብስ፡ምን፡ማድረግ፡ይገባል።

ምላሽ፤ ቍርባን፡ከግዚር፡ያዋሕዳል፤ ዕለት፡ዕለት፡ጸጋ፡ይጨምራል። ለመቍረብም፡ንስሓ፡መግባት፥ራስን፡ለቄስ፡ማስፈተን፥ኃጢአትን፡ሳይከፍሉና፡ሳያመካኙ፡ገልጦ፡መንገር፥በሠሩት፡ኃጢአት፡ማዘን፡

www.ethiopianorthodox.org

ማልቀስ፥የኀስሐ፡አባት፡የሰጠውንና፡ያዘዘውን፡ጾም፡ጸሎት፡ቀኖና፡ መፈጸም፡ያሻል።

## ፱ኛ፡ክፍል።

## ምስጢረ፡ትንሣኤ።

ጥያቄ፤ ትንሣኤ፡ማለት፡ምን፡ማለት፡ነው።

ምላሽ፤ ዘይቤው፡ከሞት፡መነሣት፥ከመቃብር፡መውጣት፥መታደስ፡መለወጥ፤ ወይም፡ሐዲስ፡ሕይወት፡ማለት፡ነው። የትንሣኤም፡ነገር፡ እንዲህ፡ነው፤ጌታችን፡ተሰቅሎ፡በሞተ፡በሦስተኛው፡ቀን፡ነፍሱን፡ ከሥጋው፡አዋሕዶ፥ሞት፡የማይስማማው፡ዳግመኛ፡የማይሞት፡ ኹኖ፡ረቂቅ፡ታድሶ፡በኀቱም፡መቃብር፡ተነሥቷል። አመ፡ሣልስት፡ ዕለት፡ሠጣ፡ለነፍሱ፡ውስተ፡ሥጋሁ። ወረሰዮ፡ትንሣኤሁ፡በመንፈስ። ወቦአ፡እንዘ፡ዕጹው፡ኆዋኅው፡ከመ፡ይክሥት፡ግብሮ፤ እስመ፡ለሥ ጋ፡ገዚፍ፡ረሰዮ፡ደቂቀ። ወአጠየቀ፡ከመ፡ውእቱ፡ርኁቀ፡እምግዘፍ፡ እንዳለ፡(ቅዱ። ሃይ፡አበ፡ኤፊ። አሬ)።

ጥያቄ፤ ነፍሱን፡ከሥጋው፡አዋሕዶ፡ማለት፡ስለ፡ምን፡ነው።

ምላሽ፤ ሲሞት፡ነፍስና፡ሥጋው፡ተለያዩ፡እንጂ፤ አካሉ፡መለኮቱ፡ከነፍስም፡ ከሥጋም፡አልተለየምና፤ በማሕፀን፡እንደ፡ተዋሐደ፡አለና፤ ስለዚህ፡ ነው። ከትንሣኤውም፡በኋላ፡እስከ፡፵ቀን፡ድረስ፡ያለፈውን፡እያላ ሰበ፥የሚመጣውን፡እያስገነዘበ፡ለበውክጡ፡እያለ፡ሲሰብክና፡ ሲያስተምር፡ቈይቶ፡ባ፵ኛው፡ቀን፥ ወናሁ፡እፌኑ፡ለክሙ፡ተስፋሁ፡ ለአቡየ፤ አንትሙሰ፡ንበሩ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡እስከ፡ትለብሱ፡ኃይለ፡ እምአርያም። ወእምዝ፡ሖሩ፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፤ ወስብኩ፡ወን ጌሎ፡ለኵሉ፡ፍጥረት፡ብሎ፡አዟቸው፥በአንብሮተ፡እድ፡ባርኳቸው፡ እያዩት፡በሥጋው፡ዐረገ። ካረገም፡ባ፲ኛ፡ቀን፡መንፈስ፡ቅዱስን፡በነ ፋስ፡አምሳል፡በእሳት፡አርአያ፡ላከላቸው፤ ሐዋርያትም፡መንፈስ፡ ቅዱስን፡ተቀብለው፥ፍሩሃን፡የነበሩ፡ጥቡዓን፡ኾኑ፤ ከብሉያት፡ ታደሱ፤ በአእምሮ፡ጐለመሱ፤ ቋንቋን፡ኹሉ፡ዐወቁ፤ ምስጢር፡ጠ ነቀቁ። ኋላም፡በምጽአት፡እኛን፡በሥልጣኑ፡ለማስነሣት፥ንዑና፡

ከምሉ፡ በክፍሉ፡ ኩብዙ፡ በጥቂቱ፡ ይህ፡ ነው፤ ከዚህ፡ የቀረ ውን፡ ሕግና፡ ሥርዐት፡ የቤተ፡ ክርስቲያንን፡ ትእዛዛት፥ በሬውስ፡ መንፈሳዊና፡ በፍትሕ፡ መንፈሳዊ፡ በፍትሐ፡ ነገሥት፡ ውስጥ፥ በሲኖዶስና፡ በመጽሐፈ፡ ኪዳን፡ ተመልከት።

ያለቃ፡ ዕንቍ፡ ባሕርይ፡ ግጥም፡ ስላሠርቱና፡ ስለ፡ ስድስቱ፡ ቃላት።

ከዐሠርቱ፡ ቃላት፡ መዠመሪያው፡ አንዱ፡
በፍጹም፡ ልቦና፡ እግዜርን፡ ውደዱ፡
ከመጽሐፍ፡ ቃል፡ ወጥቶ፡ በሰንበት፡ የሠራ፡
ዕረፍት፡ አያገኝም፡ ከሰማይ፡ መከራ።
አባትና፡ እናቱን፡ በምግብ፡ የማይረዳ፡
ተበድሮ፡ በልቶ፡ አልከፈለም፡ ዕዳ።
አልታገሠ፡ ብሎ፡ የሰው፡ ነፍስ፡ ገዳይ፡
በምድር፡ ርስት፡ ያጣል፤ ስንኳን፡ በሰማይ።
ዝሙት፡ የወደደ፡ ሞቱን፡ ማሰነብ፡ ቶቶ፡
እንስሳ፡ ነው፡ እንጂ፡ ምን፡ ይባላል፡ ከቶ።
የሰው፡ ገንዘብ፡ ሲሠርቅ፡ ልቡ፡ የማይሠጋ፡
ሲገረፍ፡ ይኖራል፡ በእሳት፡ አለንጋ።
በሐሰት፡ መስክሮ፡ በሐሰት፡ የማለ፡
ኩብርሃን፡ ጨለማ፡ ይሻለኛል፡ አለ።
ከሰው፡ ሚስት፡ የሚኼድ፡ ጠላት፡ ነው፡ ለራሱ፡
ወዲህም፡ በሥጋው፤ ወዲህም፡ በነፍሱ።
የሰውን፡ ኩብት፡ አይቶ፡ መውደድ፡ መመኘት፡
ከኵነኔ፡ በቀር፡ አያስገኝም፡ ሀብት።
መንግሥተ፡ ሰማያት፡ አትገኝም፡ ነፍሳ፡
ሰውን፡ ካሎደዱ፡ እንደ፡ ራስ፡ አድርጎ።

ስለ፡ ስድስቱ፡ ቃላት።

«ማቴ ፫፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ፲፱፡ ፲፴፡ ፲፵፡ ፲፮»

www.ethiopianorthodox.org

፻፵

ስድስቱ፡ቃላትን፡ጽሮልናል፡ከፍሎ፥
ወንድም፡ከማሳዘን፡ተጠበቁ፡ብሎ።
ለኔ፡ትኩን፡ብሎ፡የሰው፡ሴት፡ማየቱ።
እጅግ፡ፍጹም፡በዴል፡ታላቅ፡ኃጢአት።
ሳታመነዝርበት፡ሚስቱን፡የሚሬታ፥
ይፈረድበታል፡በላይኛው፡ቦታ።
በውነት፡እንኳ፡ቢኖን፡መሐላ፡ይቅር፤
ይሻለናል፡የላይኛው፡ክብር።
ክፉ፡ለሠራ፡ሰው፡በጎ፡የመለሰ።
ዘላለም፡ይኖራል፡ጽድቅ፡እንደ፡ለበሰ።
ጠላትን፡ቢወዱ፡ይወዳል፡ፈጣሪ፥
ርሱ፡ስለኾነ፡የኹሉ፡አሳዳሪ።

ያሠርቱና፡የስድስቱ፡ቃላት፡መርገፍና፡አጪዋቾች። ወንጌል፡ስለ፡ሰንዴው፡ትምርት፡በምሳሌ፡ዐዋጅ፥ ወቅሮና፡አሶቅሮ፡ያስተከለው፡ሐዲስ፡ወፍጮና፡መጅ፤ ይኸውም፡የሰምና፡ያላቢ፡ግጥም፥ላንባቢ፡ለሰሚ፡የሚጥም፥ፈላሾችንም፡የሚያስገርም።

ሰም፡አሬ፡ወርቅ፡ቀለም።

ያለ፡እየመሰለኝ፡ልጁ፡ሙቶ፡ሳለ፥
እንቡጣውን፡ባየው፡ልቤ፡ተቃለለ።
ስለ፡ደረሰብኝ፡የነሴፉግ፡ዕጣ፥
ልጄ፡ልጄ፡እላለኹ፡ደረቁን፡እንቡጣ።
አምልኮት፡ጣኦት፡የተዠመረው፥
በሴሩግ፡ነውና፡በተላላው፡ሰው።

ዐላቢ፡የፈላሾች፡ዋቢ።

ያምልኮትን፡ነገር፡ዱፍሮ፡ለመስበክ፥
አንችን፡ምን፡አገባሽ፡ከሰዎች፡ታሪክ።
ስንኳን፡አንቺ፡ላሻ፡ቤተ፡እስራኤል፥
ትታለል፡ነበረች፡በጥጃ፡አምሳል።

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፭

መንጥቆ፡ያወጣት፡ከነሬርአን፡እጅ፡
እንስሳ፡ነው፡መሰሏት፡ጥጃ፡የላም፡ልጅ።
ላም፡አሬ፡ወርቅ፡ቀለም።
ነባቤት፡ነፍስ፡ያላት፡ቁማ፡የምትኼድ፡
ያልተጋደመችው፡እንደ፡ላም፡ነገድ።
ካህንና፡መስፍን፡ሙሴ፡እያለላት፡
እግዜርም፡ቃል፡በቃል፡እያስተማራት።
በጥጃ፡ምሳሌ፡ተቷላለች፡ካልኽ፡
ብታንስ፡እንጂ፡አትበልጥም፡ከኔ፡ከላምኽ።
ወተት፡የሚሬሰው፡እንደ፡ከነዓን፡
እኔ፡አልሻልምይ፡ከዕብራውያን።
አርባዕት፡ወንጌል፡ነው፡ይህ፡የያዝከው፡ጡቴ፤
ካርባዕቱ፡እንስሳም፡ገጽ፡ላሕም፡አንቴ።
ይኸውም፡ሊታወቅ፡የንቡጣውን፡ስም፡
ልጂ፡አላለኹ፡እንጂ፤ አምላኪ፡አልልም።
ዐላቢ፡የሬላሾች፡ዋቢ።
ከነኢሳይያስ፡ከነሱቱኤል፡
ሰምቻለኹና፡እንስሳ፡እንዲሻል።
በውነትስ፡ከኾነ፡እስራኤል፡ነው፡ሞኝ፤
ዝም፡ብለኸ፡ታለቢ፤አትቀባጥሪብኝ።
ለኔም፡አንቴ፡ነው፡አርባዕቱ፡እንስሳ፡
አንደኛው፡ገጽ፡ሰብእ፡የሥጋው፡ቃል፡ጕሣ።
ላም፡አሬ፡ወርቅ፡ቀለም።
እንስሳ፡ነኝ፡ብዬ፡አርምሞ፡እንዲሊዝ፡
በጓድ፡የሚያናግር፡መጣብኝ፡ትእዛዝ።
እግዜር፡ካናገረው፡ኹሉ፡ተናጋሪ፤
ለምን፡ትለኛለኽ፡የላም፡ቀባጣሪ።
መታለብ፡መታረድ፡የላሞች፡ነውና፤

www.ethiopianorthodox.org

፻፹፪ የሚያሳዝነኝስ፡የሰው፡ድንቁርና።
የነኢዮርብዓም፡የናክአብ፡ጉድ፡
ለሰው፡ሠራሽ፡ጃጀ፡መንበርክክ፡መስገድ፡
ስንፍናው፡ሢራክን፡ያስደነገጠው፡
ሰሎሞንም፡ቢኾን፡እንዲክአብ፡ነው።
ካብርሃም፡አኗዋ፡የተገኘው፡ወርቅ፡
አንድ፡ኪሎ፡አይመሳም፡ቢመዘን፡በጽድቅ።
ዐሳቢ፡የፈላሾች፡ዋቢ።
እንዲህ፡የምትዘልሠው፡ላሚቱ፡ሰውን፡
እድግት፡በለዓም፡አትሽ፡ናት፡ይኾን፡
ወይስ፡ወንድምሽ፡ነው፡እብነ፡ቢታንያ፡
ጌታችን፡የጠራው፡ተቀምጦ፡ባህያ።
ከወተትሽ፡ይልቅ፡ነገርሽ፡ጥሞኝ፡
ልቤ፡ወደንች፡ልብ፡ተማሬከብኝ።
ከሰማይ፡በሰማው፡ድምፅና፡ንባብ፡
እንደ፡ተማረከ፡የጳውሎስ፡ልብ።
ላም፡አሬ፡ወርቅ፡ቀለም።
ትውልዷን፡ነገዷን፡ምን፡አጠያይቆኝ፤
ዝም፡ብለኝ፡ዕለበኝ፡በኹለት፡እጅኝ።
ነገሬም፡ከጣመኝ፡እንደ፡ንብ፡እንጀራ፡
ለአይሁድ፡ጋታቸው፡ከወተቴ፡ጋራ።
የኔን፡ወተት፡መጋት፡እንዲያሻቸው፡ዐውቆ፡
ጳውሎስ፡በሠራው፡ባዲሱ፡ብርጭቆ።
እያሣሣቀ፡ነው፡ውሃ፡የሚወስድ፤
ገና፡አገባኝለኹ፡ከምስጢር፡ጉድጓድ።
የዳዊት፡እንስሶች፡ልብ፡የሌላቸው፡
ላሞች፡እንዳይመስሉኝ፡እስራኤል፡ናቸው፡
ዐሳቢ፡የፈላሾች፡ዋቢ።

www.ethiopianorthodox.org

ገጹ፡ ሏሐም፡ አኅቲ፡ ብለሽ፡ ስትነግሪኝ፡
ትውልድሽ፡ ነገድሽ፡ መቼ፡ ተሰወረኝ።
አንከሮ፡ ተደሞ፡ ጽዋዐ፡ ልቡና፡
አስክሮኝ፡ ነው፡ እንጂ፡ እንደ፡ ወይኔ፡ ቃና።
እንዳሣ፡ ለማጥመድ፡ የጕዲቶን፡ ሕዝብ፡
ተዘርግቷልና፡ ምላስሽ፡ መረብ።
አለፈርፃን፡ አምላክ፡ አላንዱ፡ አለሙሴ፡
ከስሳው፡ እልፍ፡ አጋር፡ ማነው፡ ያንቺ፡ ሞክሴ።
ሽካራው፡ ምላስሽ፡ ከኔ፡ ሲሟገት፡
እንደ፡ ሮማው፡ ፓፓ፡ የማይሳሳት።
እንዲያሳሳትም፡ በሽካራነቱ፡
መጣፍ፡ ያጕርሠዋል፡ እሱ፡ ባለቤቱ።
ለናቡቀለምሲስ፡ ለነሕዝቅኤል፡
እንዳጕረሣቸው፡ አንዳንዱን፡ ጥቅል።
በሆድሽም፡ እንዳለ፡ መጽሐፈ፡ ምስጢር፡
ኃሎች፡ የሚያነቡት፡ ሞራሽ፡ ይመስክር።
ንባብኪ፡ አዳም፡ የሚላት፡ ሰሎሞ፡
አንቺ፡ አይደለሽሞይ፡ ወለተ፡ እርምሞ።
የንባብ፡ ወለላ፡ የትርጓሜ፡ ማር፡
እንዲህ፡ በዝቶ፡ ሲፈስ፡ ከላሚ፡ ከንፈር።
ባፍም፡ ስለ፡ ገባው፡ ቅዱስ፡ ጢስ፡ መጽሐፍ፡
ምላሷ፡ ንብ፡ ኹኖ፡ እንዲህ፡ ሲናደፍ።
መናገርን፡ በብር፡ ዝምታን፡ በወርቅ፡
ማነው፡ ከፈላስፎች፡ የመሰለው፡ ሊቅ።

ሳም፡ አሬ፡ ወርቅ፡ ቀለም።

ወርቁን፡ ብር፡ አድርገኽ፡ ሰምን፡ ጠቀስከው፤
የፈላስፋው፡ ሐሳብ፡ እንዲህ፡ ማለት፡ ነው፤
አጥርታ፡ እንደማታይ፡ ትንቢት፡ ከሱባዔ፡

፻፶፬ እንዳይናማይቱ፡ እንዳይሁድ፡ ጉባኤ፡
በዐይኑና፡ በጆሮው፡ እያየ፡ እየሰማ፡
ጨለማውን፡ ብርሃን፡ ብርሃኑን፡ ጨለማ፡
ብሎ፡ ለሚሟገት፡ ለሚከራከር፡
ምላሹ፡ ዝምታ፡ አለመናገር።
ሲገባው፡ ሲረዳው፡ የማይመለስ፡
አቡሃ፡ ለሐሰት፡ ፍጹም፡ ዲያብሎስ።
ቅናት፡ ምቀኝነት፡ የካህናት፡ መልከኛ፡
ባለጸልፍ፡ ገባር፡ ባላጸላፍ፡ ጢስኛ።
እነዚህን፡ ኹሉ፡ ሑዳድ፡ ሲያስሖዱ፡
ስንዴ፡ ነው፡ እያለ፡ ይዘራል፡ ክርዳድ።
ሰው፡ ኹሉ፡ የሚያጭደው፡ የዘራውን፡ ነው።
በብሉይ፡ በሐዲስ፡ እንደ፡ ተጣፈው።
ለነሞት፡ አይፈሬ፡ ለነሐሰት፡ ጽድቁ፡
አእምሮ፡ ይስጣችው፡ ይህነን፡ እንዲያውቁ።

ዐላቢ፡ የፈላሾች፡ ዋቢ።

እንደ፡ ዷላድዮስ፡ እንደ፡ ቄርሎስ፡
እግዜር፡ አቅንቶልን፡ ጥያቄና፡ መልስ።
አኩን፡ እሴና፡ አንቺ፡ ባንከራከር፡
ማን፡ ይወልደው፡ ነበር፡ ይህነን፡ ምስጢር።
ስንከራከርስ፡ እኛ፡ ኹለታችን፡
አለመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ማነው፡ ፫ኛችን፡
ከመከራከርም፡ የሚገኘው፡ ጥቅም፡
ብዙ፡ ስለ፡ ኾነ፡ አይቈጠርም።
የክርክርም፡ ሐሳ፡ ፍችና፡ ጋብቻ፡
ለመረዳትና፡ ለማስረዳት፡ ብቻ።
ከዚህ፡ የወጣው፡ ግን፡ አሉታና፡ ሽፍጥ፡
የሰይጣን፡ መሣሪያ፡ ፯፡ አፍ፡ ሸጉጥ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፵፰

ጥዴቱም፡ ትርጓሜ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ዐይነት፡
የማይመሳሰል፡ ካንቼ፡ ቃሌ፡ ትምርት።
ሳም፡ አፈ፡ ወርቅ፡ ቀለም።
ወተት፡ ሳትጠጣ፡ ከነልጆችኽ፡
ጊዜው፡ በክርክር፡ ስላለፈብኽ።
ያንተም፡ የኔም፡ ነገር፡ በዚሁ፡ ይቁም፤
ላሞች፡ ብንበልጥ፡ እንጂ፡ ከሰው፡ አናንስም።
በተፈጥሮም፡ ቢኾን፡ እኛ፡ እንቀድማለን፡
ከሰው፡ አባት፡ እናት፡ ካዳም፡ ከሔዋን።
የተሰጠንም፡ ሕግ፡ የባሕርይ፡ ምሰሶ፡
ዝልፍልፍ፡ አይልም፡ እንዳዳም፡ ላንቆሰ።
ዐሳቢ፡ የፈላሾች፡ ዋቢ።
እንስሳን፡ ለመሢዕት፡ እግዜር፡ የመረጠ፡
ለካ፡ በዚህ፡ ኑሯል፡ እኹን፡ ተገለጠ።
ከንቅልፌ፡ ሳልነቃ፡ በሰው፡ ልጅነቴ፡
ሕልም፡ ይመስለኝ፡ ነበር፡ የላም፡ ልጅ፡ ትምርቴ።
ስላይሁድ፡ ስላዳም፡ በተቸሸው፡ ትች፡
ሥጋዩ፡ ብትራብ፡ ነፍሲ፡ ጠግባለች፡
ብሉይ፡ ሰው፡ ሲቀምሰው፡ ይህን፡ ሐዲስ፡ ወጥ፡
ተከንፈሩ፡ ጋራ፡ እጁን፡ እንዲመጥ።
ከብሉይ፡ ቆንጥረሽ፡ በሐዲስ፡ ግራም፡
ጥቂት፡ ጨምረበት፡ የታሪክ፡ ቅመም።
ሳም፡ አፈ፡ ወርቅ፡ ቀለም፡
ምንም፡ ቢጭኑባት፡ የጠያቂ፡ ወስኩ፡
ለላም፡ ታሪክ፡ ቀንዷ፡ አይከብዳትም፡ እኮ።
ባፍኒ፡ በፊንሐስ፡ ጦስ፡ በነዒሊ፡ ዳፉ፡
የእስራኤል፡ ዐይን፡ ካህን፡ ስለ፡ ጠፋ።
በሳሙኤል፡ ዘመን፡ በታላቁ፡ ዒሊ፡

www.ethiopianorthodox.org

፻፵፯
እስካቢዳራ፡ቢት፡ከምድረ፡ኢሎፍሊ፡
ታቦት፡ጽዮንን፡የተሸከሙት፡
ላሞች፡አይደሉምይ፡የግዜር፡ካህናት።
ዖዛስ፡ደፍሮ፡ቢቀርብ፡ታቦት፡ሊደግፍ፡
ማን፡ወግቶ፡ገደለው፡በቀንደቹ፡ጫፍ።
ስንኳን፡ላሞቹ፡እኛ፡ማደሪያችን፡ጎሌ፡
በጌታችን፡ልደት፡ቅዱስ፡ተብሏል።
ካይሁድም፡አብልጦ፡እኛን፡ለመውደዱ፡
ሥስት፡ምስክር፡አለኝ፡በጎል፡መወለዱ፤
ካህያና፡ከላም፡እስትንፋስ፡መውሰዱ፤
ሰብአ፡ሰገልንም፡በዚያው፡ማስገዱ።
በበረት፡ሲወለድ፡መድኅኔ፡ዓለም፡
ዐልጋውም፡ዙፋኑም፡የደንጊያ፡ግርግም፡
ነቢዩ፡ሚክያስ፡ከዳዊት፡ጋር፡ቆሞ፡
በትንቢት፡መኘረቢያ፡የጠረበው፡ቀድሞ።
ዳንኤልና፡ዕዝራም፡ሸካራ፡እንዳይኾን፡
በሱባዔ፡ወቀረው፡የቀቡት፡ዘመን።
ስንኳን፡በምድርና፡በሰማይ፡ውዱድ፡
አርባዕቱ፡እንስሳ፡የዙፋኑ፡አዕማድ።
እናትና፡ልጁም፡የበረት፡ውሉዶች፡
ስማቸው፡የእንስሳ፡እንቦሳና፡ግች።
ማሰዲ፡ሲወጡ፡ከበረታቸው፡
ሔኖክ፡እንደ፡ዮሴፍ፡ቀርቦ፡ያያቸው።
ኋላም፡የተሸጠው፡ለሺ፡ብር፡
ከበረት፡ሲወጣ፡ሔኖክ፡ያየው፡ሶር።
ቀንዱ፡ሰማይ፡ጠቀሰ፡ጭራው፡ምድር፡አበሰ፤
ስሙም፡ርጎ፡ዐይሮ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
የዲግማ፡ተንሣይ፡ሌት፡ለልጅ፡ላዋቂው፡

www.ethiopianorthodox.org

ብሉት፡ ጠጡት፡ ብሎ፡ ቄስ፡ የሚያቀርበው።
ክፍሉ፡ ዮሐንስም፡ የዘላኖች፡ ዳኛ፡
ሲፈርድና፡ ሲተች፡ ሲመሰክር፡ ለኛ፡
የፈረደውን፡ ፍርድ፡ በመወድስ፡ ቅኔ፡
እጠቅስልሃለሁ፡ በቃሌና፡ ባይኔ።
የተቀረጸውም፡ የቅኔው፡ ማኅተም፡
ካኅቴ፡ አንጥረኛ፡ ከሉቃስ፡ ዘላሕም።
መርገጫውም፡ ንባብ፡ የቀለሙ፡ ሐብር፡
እግዚር፡ የቆመበት፡ የዳዊት፡ መዝሙር።

እምከዊነ፡ ካህን፡ ዲዲይስ፡ ከዊነ፡ ኖላዊ፤
ወኀለ፡ እንስሳ፡ ትትበዴር፡ እምቤተ፡ መቅደስ፡ ዐባይ፤
እስመ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ኮነት፡ ቤተ፡ ፈያታይ፤
ወበላዕለ፡ ኖሎት፡ ኢሀለወ፡ ላዕለ፡ ካህናት፡ ዘሀሎ፡ እከይ፤
ትእምርተ፡ ዝኒ፡ ከመ፡ ንርአይ፤
በኀለ፡ እንስሳ፡ ሠረቀ፡ ዘኢየዐርብ፡ ፀሓይ፤
ወኖሎት፡ ተዘውዑ፡ ምስለ፡ ሐራ፡ ልዑል፡ ሰማይ።
ዐዲ፡ እምቅድመ፡ ዝኒ፡ እመካነ፡ ኖሎት፡ ወመራዕይ፡
ከመ፡ ተጸውዑ፡ ዳምፀ፡ እግረ፡ ቃለ፡ ዜና፡ ሠናይ፡
ወልዱ፡ እንበረም፡ ለምስፍና፡ ወለቀብዐ፡ መንግሥት፡ ወልደ፡ እሴይ።

ፈላ፡ እንዲሉኽ፡ ዲግሞ፡ ጠይቀኝ፡ ልመልስ፤
እንዲፈሉኽ፡ ግና፡ አሬን፡ በጪው፡ አብስ።
ዐሳቢ፡ የፈላሾች፡ ዋቢ።

ኦ፡ ላሕምየ፡ ዲብተራ፡ ኦሪት፥ ቅድስት፡ ቅዱሳን፡ አልሕምት፤ ዘማኅዴረ፡ መጽሐፍ፡ ክርሥኪ፡ ወሙዳየ፡ ቀለም፡ ቀርንኪ፥ ተክዕወ፡ ሞገስ፡ እምከናፍርኪ።

ከብሉይ፡ ከሐዲስ፡ በጠቀሰው፡ ቃሉ፡
ታሪክሽ፡ ከዋታል፡ ፕያቄዎን፡ ኹሉ።
እንግዲህስ፡ ወዲህ፡ ወርቅ፡ ይኹን፡ ዝምታ፤

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ዘበሾቻቸው፡ብሎይ፡ሐዲስ፡— ስላነሣሡት፡ኹነው፡በሳስ፤
ፍትሐ፡ነገሥትም፡ቄሳጤ፡ሊቁ፡—አይዞኽ፡ስላለው፡በፍትሐ፡ጽድቁ፡
በተሟጋቾች፡አስፕ፡አገባ፡— ዳኝነታቸው፡ስለ፡ተዛባ፡
በግዜር፡ዳኝነት፡ሲመረመሩ፡—ክረበናት፡ነው፡የሚቈጠሩ፤
መቼ፡ከሙሴ፡ከዳንኤል፡— ከማይዘቡት፡በፍርድ፡ቃል፡
ሰይፍ፡ይፍረድብን፡ብለው፡ሲቀኙ፡—እንዴት፡ይታዘብ፡ያ፡ባለሰይፉ፡
ዮሐንስ፡ያየው፡በራእይ፡ሰልፍ፡— ካፉ፡ሲመዘዝ፡፪፡አፍ፡ሰይፍ።
ዐይኖቹውንም፡የሚያባርቅ፡— የጕሮ፡ቅኔ፡ሠምና፡ወርቅ፡
መምህር፡ሲዘርፈው፡ባለወንበሩ፡— የሚሻማበት፡ደቀ፡መዝሙሩ።
የግዜር፡አገባብ፡ቅዱስ፡መጽሐፍ፡—ይህን፡ዘረፋ፡ወየው፡ሲነቅፍ፤
የሚያስገመድል፡ፍርድ፡እንደ፡ዳቦ፡— ማነው፡ይባላል፡አላቆ፡ጕቦ።
ዳባውንስ፡ፍርድ፡ሲገመድሉ፡— ጋኑንም፡ወንጌል፡ሲያዘነብሉ፡
እንደ፡ሰው፡ቍሞ፡በማኽላቸው፡— ማነው፡እልግዜር፡የሚዘልፋቸው።
ዘለፋውንም፡ላታይ፡ብቶድ፡— መዝሙር፡ተመልከት፡በሰማኒያ፡አንድ፤
ከሠር፡እስከ፡ጫፍ፡ያለው፡ንባብ፡—የዳኞች፡ርባ፡ስምንት፡መደብ።
መዝሙሩን፡ቃኝቶ፡የሚመራው፡— ምንት፡ይበቅዓሙ፡አለ፡ከዚያው፤
አቋቋሙንም፡የሚያሳየችው፡— የልብ፡ጽኑት፡ግራ፡ጌታቸው።
(ተረት፤ ተሹሞ፡ከመታለል፡ፕሎ፡መኰብለል)።
ይበል፡የሚያሠኝ፡የኰብላይ፡ቅኔ፡— ስሙ፡መወድስ፡ግብሩ፡ምናኔ፡
ያለምን፡ክብደት፡በግፉ፡ንምራ፡— የሚያመዝዝን፡ከገዳም፡ጋራ።
ቀሊል፡ውእቱ፡ዕጸበ፡ገዳም፤
ቅድመ፡ግፍዐ፡ዝንቱ፡ዓለም፡አርአያ፡ጽላሎት፡ወጢስ።
ወነያ፡ይእቲ፡በዓልተ፡ፕዒና፡ሐዲስ፤
ምስለ፡አራዊት፡ዘተኃድር፡ነፍስ፡
እንዘ፡እምነ፡ሰብእ፡ትትገሐሥ፤
እስመ፡ግዕዘ፡አርዌ፡ዐቢይ፤ ወግዕዘ፡ሰብእ፡ንኡስ።
በመብልዕስ፡ኀበ፡እከይ፡ዘያበጽሓ፡ለከርሥ፡
ጸላኤ፡ማርያም፡ወሳዲትከ፡ምስለ፡ዲቂቀ፡ኢዱም፡ይትባአስ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፵፯

አልበቃኽ፡ብሎት፡የሰጡት፡ምስ፡ — ከገቢው፡ኹሉ፡የሚያነሣሣ፣
አምኖም፡ለሾመው፡ለዴጉ፡ጌታ፡ — የማይታመን፡ዱሩር፡አውታታ፣
ገበሬ፡መስሎም፡በሳሬ፡እንቅብ፡ — ጕቦ፡የሚዝቅ፡ካውድማ፡ሕዝብ።
ይሁዳ፡ማለት፡እሙን፡አማኒ፡ — ያሠራንዱ፡ነገድ፡መስፍን፡ኰናኒ፣
እናቱ፡ልያ፡ስትሳይመው፡ — የአብርሃም፡ድድቅ፡እንዲስማማው፡
ቡራኬ፡ይስሐቅ፡ወያዕቆብ፡ — ያዴረኙበት፡ፕሩ፡መዝገብ፣
የኮከብ፡ምሥራቅ፡ያንበሳ፡ጐሬ፡ — የወንድሞቹም፡አላባሽ፡አግሬ፣
ታላቅ፡ወንድምን፡ጋሼ፡ማለት፡ — ከዚህ፡ይመስላል፡የወጣበት።
ያይሁድ፡መሪ፡የስም፡ይሁዳ፡ — ጌታውን፡ሸያጭ፡ባለብዙ፡ዕዳ፣
አባቱን፡ስልቦ፡እናቱን፡ማርኮ፡ — ሚስት፡ያዴረጋት፡እርሱ፡ነው፡እኮ፣
ለንዴና፡ክርዳድ፡ስሙና፡ግብሩ፡ — በሹመት፡ሳሬድ፡አስኪበጠሩ፡
ተበፕረውም፡ስለተለዩ፡ — ርስ፡በርሳቸው፡እየታበዩ፡
ስሙ፡ዐማትና፡ግብሩ፡ምራት፡ — ሳይስማሙ፡ወዴ፡መሬት።
መርሬና፡ሬትል፡ስሙ፡ይሁዳ፡ — አልጠቀመውም፡ይህን፡ቀዳዳ።
ማትያስማ፡የርሱ፡ወራሽ፡ — ገባሬ፡ሠናይ፡ሹመት፡ቀዳሽ፣
ዕጣው፡በርሱ፡ላይ፡ስለ፡ወደቀ፡ — የተኰነነው፡ሹመት፡ጸደቀ፣
ጸድቁም፡ሹመት፡ሲሰኝ፡ሳይናማ፡ — ከብርሃን፡በቀር፡የለም፡ጨለማ።
ሳይናማውም፡ሹም፡ለገብር፡ኄር፡ — ጠላት፡የለውም፡አለሹም፡ሽር፣
ሞትም፡ቢሽረው፡እንደ፡ቀዳሚ፡ — ዳግም፡ይሾማል፡በእሑድ፡ዕድሜ፡
ተግሣጽ፡የሚያጠግብ፡ለሆዳ፡ሰሬ፡ — ያባቶቻችን፡ቅኔ፡አሳሳሬ፡
ባርብ፡ውሃ፡ታኮቦ፡ኹለት፡እጁን፡ — እንሆ፡ቁሻል፡ከሬታችን።

ዋዜማ፣ ያንከበር፡ዐይናማ።

በሀብት፡ኢይትዓረቁ፡

ሚካኤል፡ሕያው፡ወመልአክ፡ሐሰት፡መዋቲ፣
ክልኤሆሙ፡እስመ፡ተራከቡ፡በሢመት፡አሐቲ።
ወእመ፡አርኣያ፡ናመጽእ፡እምውስተ፡ዓለማት፡ክልኤቲ፥
ሢመት፡ለኵሉ፡እንዘ፡ፀር፡ይእቲ፥
መኳንንት፡ይትጋደሉ፡ባቲ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፵፯

ዓዲ፡ ሠላሴ፡ ቅድስት፡ ዘበዐውዲ፡ መስቀል፡ ወንጌል። ዐይናማው፡
ደጃዝማች፡ ወልዴ፡ ገብርኤል፥ ምናቴ፡ ባሻሸው፡ በሐዲስ፡ መንፈስ፡ ቅሌ።
ካረጋዊ፡ ፈልፈል፡ ከሬልክስዩስም፡ ጠል፥ ከማር፡ ይሠሐቅም፡ ወለላ፡
ቃል፥ እያለቀሱ፡ ተጐንብሰው፡ የቀዱት፡ ጠበል።

ዓለም፡ እስከ፡ ጊዜሃ፡
በሐብለ፡ ዝንጓዌ፡ ትስሕበኒ፤
ወታወርደኒ፡ ካዕበ፡ ይእዜ፡ ኀበ፡ ዘቀደሚ፡ መርገም፡
ለዘተወለድኩ፡ በሥጋ፡ ወደም።
ዘአእመራስ፡ ጠቢብ፡ ሰባዊ፡ ለኅልፈተ፡ ዘቲ፡ ዓለም፡
ፍዲ፡ ወይን፡ ይስተይ፡ ማየ፡ ዝናም፤
ወህየንተ፡ ልብስ፡ ይትከደን፡ ቈጽለ፡ አዕዋም፤
እስመ፡ ዛቲ፡ ጽላሎት፡ ወሕልም።

የሠላሴ፡ ጭላጭ፡ መወድስ፡ የድሆችና፡ የባለጠጎች፡ ፈውስ፤ እንዘ፡ ነዳይ፡
ዕቡይ፡ እንዘ፡ ባዕል፡ ቂቁይ፡ ለተባሉቱ፡ በስተኞች፥ ከብሉይ፡ ፍርድና፡ ከሐ
ዲስ፡ ትች፥ በርሳቸው፡ አንደበት፡ ተመዝና፡ የተቀመመች።

ትምክሕትከ፡ ኅድግ፡ ብእሲ፡ ዓለም፤
ወቀለመ፡ ትዕቢት፡ ኢትጽሐፍ፡ ውስተ፡ ልብከ፡ ክርታስ።
አምጣኒ፡ አኮ፡ በጽድቅ፡ ተጸግዎ፡ ሲሳይ፡ ወልብስ፤
ወአኮ፡ በኃጢአት፡
እምብዕለ፡ መንግሥት፡ ዘትጼነስ፡ ነፍስ፤
በሐብለ፡ ሃይማኖት፡ ዘትትዋረስ፡
ርስት፡ ዮርዳኖስ፡ እማ፡ ወርስት፡ አቡሃ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ።
ብዕለስ፡ እመ፡ በጽድቅ፡ ወበኃጢአት፡ ተጽናስ፥
አክአብ፡ እንዘ፡ ሀሎ፡ እምኢተጸነሰ፡ ኤልያስ፤
ወእምድኅረ፡ ዝንቱ፡ ነገር፡ እምኢወሀበ፡ ክርስቶስ፡
መርኆ፡ መዝገበ፡ ወርቅ፡ ለይሁዳ፡ ወመርኆ፡ ሰማይ፡ ለጴጥሮስ።

የሚመጣውም፡ ካለፈው፡ ጋራ፡ — ድርብ፡ ይባላል፡ በጥበብ፡ ሥራ፤
ነጠላም፡ ቢሉት፡ በድርብ፡ ፈንታ፡ — ምስጢሩ፡ ግጥም፡ ይኾናል፡ ኩታ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፷፯

አንዴ፡ባሕርይ፡ማለት፡ኋላ፡የመጣ፡—ያውጣኪ፡ኩፍኝ፡ወይም፡ሬንጣጣ፤
ዐይን፡የሚያበልዝ፡እብነ፡ቱሳሒ፡— የተዋሕዶ፡ማሕረጽ፡መድሐ።
፪፡አርአያም፡፪፡አካል፡— ጌታና፡ሎሌ፡ያንጊያና፡ቅል፡
እየብቻቸው፡ሠራ፡ሲሠሩ፡— እንዴ፡መንታ፡ልጅ፡የሚጫሬኑ፤
፩ኛው፡አምላክ፡ታምር፡አድራጊ፡— ፪ኛው፡ሰው፡በጦር፡ተወጊ።
በአብ፡አዋጅ፡ግን፡በማርያም፡— ልቡስ፡ሥጋ፡ወልድ፡ዋሕድ፡ዐፅም፡
የነጳውሎስ፡የነሔሮክ፡— ወልዴ፡ብእሲት፡ሥጋው፡አምላክ፤
በሰውነቱ፡ርቦት፡ጠምቶት፡— እንደይመጠምኝ፡የናቱን፡ጡት፡
እነዚህ፡ኹሉ፡ጡት፡አስጣዮቹ፡— ጠላቶች፡ናቸው፡መች፡ወንድሞቹ።
ምንታዌ፡ባሕርይ፡ዋሕድና፡አካል፡— እንደይናወጥ፡ከሥጋው፡ቃል፡
ዋሕድነቱ፡ለብሶ፡ብኵርና፡— ዳግማይ፡አዳም፡ተብሏልና።
የማርያምን፡አንዝት፡ሲያርሱ፡— አብን፡ከሰማይ፡እየጠቀሱ፡
አባቶቻችን፡እነተዋኔ፡— የሴት፡ልጅ፡ብለው፡የሰጡት፡ቅኔ፡
ስሙ፡መወድስ፡የጐንደር፡አፋ፡— የተመዘዘ፡ከወልዴ፡ኬፋ።
በዘሞቱ፡ወልድ፡ወበዘኢሞቱ፡
ክልኤቲ፡አንስት፡ለእመ፡አንሥአ፡ቅሥት፡
ወእመ፡ለፍትሕ፡ሖራ፡ኀበ፡ሰሎሞን፡አብያተ፤
ሰሎሞን፡ይቤ፡ይግበራ፡ክልኤተ፡
ወልደ፡ዘኢሞተ፡
ከመ፡በኅንቱ፡ያጠይቅ፡ጽድቀ፡ወሐሰተ።
እብሰ፡ወማርያም፡እንዘ፡ኢይትናገሩ፡ምንተ፡
ወነገረ፡ቅሥት፡ኢያንሥኡ፡በዘሞተ፡ወኢሞተ፡
እስመ፡እምንእስከ፡ልዩን፡መፍቀሬ፡ነገር፡አንተ፤
ከሬልከ፡ኀበ፡ክልኤ፡ሥግወ፡መለኮት።
የልዩን፡ክታብ፡ይህ፡ነው፡መቅድሙ፡— የተጣረበት፡ኅቡእ፡ስም፡ቂሙ፤
ንስጥሮስ፡ዐርሮ፡ምድር፡ሲያዝ፡— ስለ፡ተነሣ፡ያውጣኪ፡ጊዝ፡
ከኤሬሶኑ፡ኛቂት፡ዝቅ፡ያለ፡— ስሯጽ፡ጉባኤ፡በማኽል፡አለ።
መቼም፡አለጽርጁ፡አለባሪክ፡— ከሌላ፡አይበቅልም፡መናፍቅ፡ሠክ፤

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፱

ባሠርቱ፡ቃላት፡የታሰሩ፡— አዕማደ፡ምስጢሩ፤
ከሔኖክ፡ግእዝ፡ከሲናይ፡— እስከ፡ሳብዕ፡ሰማይ፡
ብሉይ፡ተሐዲስ፡ዕርከኖቹ፡— ለወጭ፡ለወራጅ፡እንዲመቹ።
በብሉይ፡ኪዳን፡በሐዲስ፡— እኛን፡ሊባርክ፡ሊቀድስ፡
የቀዳሴውም፡ጠበል፡— ኦሪትና፡ወንጌል፡
ካብርሃም፡ዛፍ፡የነቃው፡— ዐይነ፡ትምርት፡ውሃው፡
ባዳም፡ራስ፡ቅሉ፡ሲቀዳ፡— ማየ፡ሕይወት፡ጸዐዳ።
የስሙ፡አጠራር፡አዶናይ፡— የሥላሴን፡መልክ፡የሚያሳይ፥
ምንም፡ቢረግጠው፡ፍራማስ፡— አይታይም፡ዱፍርስ።
የማይደፈርስ፡የማያድፍ፡— በሊቃውንት፡ኰርፍ፤
ያበጠው፡ንባብ፡ዕብራይስጥ፡— በትርጓሜ፡ሲፈርጥ፥
አዶናይ፡ማለት፡ጌቶቼ፡— እኔ፡እንዳየኹ፡ገብቼ፡
ይሁዲ፡ግብጦ፡ያሳያት፡— የአብርሃም፡በአት።
አዶናይንም፡የመሰለ፡— ኤሎሂም፡ከዚያው፡አለ፤
ኤሎሂም፡ማለት፡አምላኮች፡— በዕብራይስጥ፡ፍቾ፤
ለመከብባቸው፡ለወንጌል፡— እንደ፡ሳብአ፡ሰገል፡
ኦሪት፡ነቢያት፡በፍሥሓ፡— ያቀረቡት፡አምኃ፡
የሥላሴ፡ወርቅ፡ዕጣን፡ከርቤ፡— የኹለቱም፡ዘይቤ።
የግእዝ፡ወንድም፡ዕብራይስጥ፡— ቃልኽን፡የማትለውጥ፡
ኤሎሂም፡ያሉት፡አነሙሴ፡— አላዳኖይ፡ሥላሴ፡
ማነው፡ይባላል፡ባንተ፡ዘንድ፡— እስኪ፡መስክር፡ፍረድ።
(ተሰጥወ፡ዕብራይስጥ፡ወይቤ፥ ለዘጸውዖ፡በይባቤ)።
እንደ፡ቀደሩ፡እንደ፡ሐና፡— እኔ፡መች፡አዋሽና፤
በነአብርሃም፡ቃል፡ኪዳን፡— እኔ፡ባሏ፡ስኾን፥
ለቤት፡አይሁድ፡ባለቤቱ፡— አልገባትም፡ትምርቱ፤
ቢገባትማ፡እንዳንተ፡— ነገር፡በተከተተ።
አዶናይና፡ኤሎሂም፡— የይሁዲ፡ልጊም፡
በሮቱ፡ቅዱስ፡አወንታ፡— አሉታዋን፡ሊገታ፡

፶፮

ከሬዳሌ፡ ማዕዷን፡ ከሂኖስ፡ — ከነቢያት፡ ራስ፡
ቀድሞ፡ የሠራው፡ እግዜር፡ — መጻሕፍትን፡ ሊፈጥር።
ከኦሪት፡ ዝናም፡ ከርግማን፡ — እንደ፡ ጳውሎስ፡ ለመዳን፡
አንገባም፡ ብለው፡ ከዚች፡ ዋሻ፡ — ይሁዲና፡ ፈላሻ፡
ብኵርናቸውን፡ ለኛ፡ ሼጡ፡ — እንደ፡ ዔሳው፡ ሲቀብጡ።
አለቀቻቸው፡ እነሐና፡ — የሼጡትን፡ ብኵርና፡
ዛሬ፡ ቢኛ፡ ላይ፡ ሲያዩት፡ — እንዴት፡ ይቀኑበት፤
እኛ፡ ነንና፡ ይሥሐቅ፡ — የአብርሃም፡ ዱቂቅ፡
ስለ፡ ተወለድን፡ በመሐላ፡ — ከይስማኤል፡ በኋላ፡
በጉን፡ ሠውቶ፡ በጽዮን፡ — እግዜር፡ የተቤዠን።
ማኅበራችንም፡ ያዕቆብ፡ — የቡራኬው፡ መዝገብ፥
አዕቃዴ፡ ክሕደት፡ ሰኮና፡ — በሰዋስው፡ ጕዳና፤
በመጻሕፍትም፡ አካኼድ፡ — አይቀድሙትም፡ አይሁድ።
መልክ፡ ሥላሴ፡ መልክ፡ እየሱ፡ — በተዋሕዶ፡ ለማድረስ፡
እንደ፡ አብርሃም፡ ጊዜ፡ ቀትር፡ — ቁመን፡ ከዛፉ፡ ሥር፡
ባሕርዩን፡ በሥር፡ በነቅ፡ — በማይነቃነቅ፡
አካሉንም፡ ባጽቅ፡ በመትረብ፡ — ከሥሩ፡ ከነቅ፡ በሚሳብ፡
እየመሰልነ፡ ኑ፡ እንሰበክ፡ — ስለ፡ ሕያው፡ አምላክ።
የምንሰብከውም፡ የቃል፡ ዛካ፡ — በኢታምልክ፡ ሊለካ፡
አንዱን፡ በቀል፡ ዛፍ፡ መለኮት፡ — ባለሦስት፡ አዕጹቅ፡ ማለት፤
ያጽቆችም፡ ድምር፡ ከነጕንዱ፡ — እንዘ፡ ሠለስቱ፡ አሐዱ፤
የመትረቦችም፡ ከነነቁ፡ — እንደ፡ ጕንዱና፡ እንዳጽቁ።
እንዳይሰበር፡ ይህ፡ ምሳሌ፡ — የሃይማኖት፡ ብርሌ፡
በየልባችን፡ ይከተት፡ — ዳግመ፡ እንዳንጠጣበት።

ክፍል፡ ካልእ።

በእንተ፡ አሐዱ፡ አካል፡ ዐማኑኤል፡ ዘበትርጓሜሁ፡ አምላክነ፡ ወስብእ፡ ዘይትለአክ፡ ውስተ፡ ዱብተራ፡ ስምዕ፡ እንተ፡ ኢገብራ፡ እደ፡ ሰብእ፤ እስመ፡ ለሊሁ፡ ካህን፡ ወለሊሁ፡ በግዕ፤ ለሊሁ፡ መሢዕት፡ ወለሊሁ፡

www.ethiopianorthodox.org

፻፺፮

ሲሬሳውና፡ሲገሣው፡ — ሳለም፡የሾተተው፥
ኹሉ፡አፍንጫውን፡እስኪይዝ፡ — ርኩም፡እስኪወገዝ።
፩፡ባሕርይ፡የሚል፡ሰባኪ፡ — ያውጣኪ፡ልጅ፡ነው፡ያውጣኪ፤
የባሕርይ፡ግብሩስ፡ልዩት፡ — ክልኤቱ፡ሲባል፡በውነት፡
ማነው፡የሚለው፡፩፡ግብር፡ — ካውጣኪ፡ልጅ፡በቀር።
ሐኖክ፡ያያቸው፡በራእይ፡ — ሙሴም፡በነቅዐ፡ማይ፡
ሰባ፡ኹለቱ፡አልሕምት፡ — ክቡዳኒ፡አቅርንት፡
ዐሠራ፡ኹለቱም፡ዝሞኖች፡ — ጥርስ፡ረዣዥሞች።
ታላቁ፡ዝሆን፡ይህታ፡ — ፍለጋውም፡ሐተታ፥
ኩንቢው፡ሃይማኖት፡አሐቲ፡ — እንዲትባል፡ክልኤቲ፡
ቃል፡ሥጋ፡ኮነን፡በአርምሞ፡ — አንብቦና፡ተርጒሞ፡
ሞተ፡በሥጋ፡ሲልኽ፡ — ፍችው፡ምን፡መሰለኽ።
ሥራው፡መሣሪያው፡፪፡ክፍል፡ — ሠሪው፡ጌታ፡ግን፡፩፡አካል፤
ሥራም፡የባሕርይ፡ፍሬ፡ነው፡ — አካል፡የሚለቅመው፡
ባሕርይም፡ያካል፡መቅድም፡ — ሥራን፡የሚያስፈጽም።
የቅዱስ፡መጽሐፍ፡ትምርት፡ — ሰሌዳና፡ወንፊት፥
ምንም፡ቢለወጥ፡ቢያረጅ፡ — በነገሥታት፡ዐዋጅ፡
አያስቦካንም፡እንደ፡ግብጽ፡ — ያልተነፋ፡ሐሪጽ።
በሦስት፡ጉባኤ፡ምስክር፡ — የሃይማኖት፡ነገር፡
ሲቆም፡ሲተከል፡ሲወሰን፡ — ለስምንቱ፡ማእዝን፡
የኒቅያ፡ስም፡አርቶዶክስ፡ — የማይደመሰስ፤
ቀለሙም፡እሳት፡ተዋሕዶ፡ — ከኤሬስን፡በረዶ፡
ቍስጥንጥንያን፡በውነት፡ፍርድ፡ — የሚያነድ፡የሚያበርድ።
አወራረዱም፡ከኒቅያ፡ — ወደ፡ኢትዮጵያ፡
ያትናቴዎስን፡ማኅተም፡ይዞ፡ — በግሥገሣ፡በጕዞ፡
የማኅተሙም፡ሬዲል፡ — ከሣቴ፡ብርሃን፡ይሳል።
ጥንተ፡ስማቸው፡ዲመንሚን፡ — ሐሮጥቃ፡ሲኖን፡
እንዴት፡በዚህ፡ስም፡ይጠሩ፡ — አውጣኪና፡ማኅበሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሰንኳን፡ለመምህር፡ለተማሪ፡— ያሳዝናል፡ይህ፡ፕሬ።
ኦርቶዶክሶች፡ነን፡እያሉ፡— ኢትዮጵያን፡ካታለሉ፡
ዐይናማውንም፡ሃይማኖት፡— ዕውር፡ካደረጉት፡
ይመርመሩልኝ፡በሡላሴ፡— ዱብተራና፡መነኩሴ፡
ባርባ፡ዓመት፡ገድሮ፡ለማውጣት፡— ሐሳባድባር፡ሹመት።
ሌላ፡ዐይነት፡መጣፍ፡ሲገልጡ፡— ወንጌል፡እየረገጡ፡
አንድ፡ዐረፃ፡ንጉሡ፡ቢስቡ፡— ዱር፡የሚሰበስቡ።
ሡላሴ፡ዘድንቅ፡ማርቆስ፡ኦርቶዶክሴ።

አርዮስ፡ወመምህሩ፡
ላዕለ፡ሐዋርያት፡አመክነዩ፡
ብሂለ፡ፍጡር፡ወልድ፡በቀዳማዊ፡ልደቱ፡
ለአጽድቆ፡ሕልም፡ነገሮሙ፡ከንቱ።
ዮምኒ፡ይሬጽም፡ዐመፃ፡በመስፈርት፡አሉ፡ክልኤቱ፡
እንዘ፡ፍናዊሃ፡በኍልቈ፡ቤቱ፡
ሰብእ፡ኵሉ፡ለሃይማኖቱ፡
ይቀብዐ፡ስመ፡ምእት፡ሠለስቱ።

ክፍል፡ሣልስ።

ዲቤ፡ቴዎዶስዮስ፡ታስዓየ፡ቅዱስ፡ዲዮስቆሮስ፡ዘሳሬ፡ረሲዓን፡ እለ፡አውጣኪ፤ ወአመጽላዊ፡ገጽ፡ባህሎሙ፡ሐምለ፡መሎኪ። እመ ሰ፡ለነ፡በህላዌነ፡ዘሞእነ፡ሰይጣን፡ወእግዚአብሔር፡ቃል፡ኢነሥአ፡ ካልአ፡ህላዌ፡ዘእንበለ፡ህላዌ፡ዚአነ፥ ወረሰዮ፡ኢሐማሚ፡ወኢመ ዋቲ፡እመአመ፡ተዋሐደ፡ቦቱ፤ ከመ፡በዝንቱ፡ያስተማስሎ፡ምት ሀተ፡ወጽላሎተ፤ እመሰ፡ከመ፡ዝ፡ውእቱ፡ከንቱኪ፡ሃይማኖትነ። መኑ፡ዘኢያነክር፡እምስጢረ፡መጻሕፍት፤ ወኢይሰድዶ፡ለአውጣኪ፡ ወኢያርኅቆ፡ሎቱ፤ ወለኵሉ፡ዘይሄሊ፡እበደ።

ያውጣኪ፡ትምርት፡ሸባ፡አንካሳ፡— ያውም፡ዕውር፡ጠንባሳ፤
አለስሙ፡ስም፡ተቀብቶ፡— የዓብጽ፡ኦርቶዶክስ፡ተሠኝቶ፡
በማርቆስ፡ስም፡ትከሻው፡— ጳጳስ፡እየመራው።

፻፺፬

በኋላ፡ዘመን፡ስለ፡መጣ፡— የሰው፡ዐይን፡አወጣ።
ዳግመኛም፡ሲጣፍ፡ሲታደስ፡— ከናባ፡ማቴዎስ፡
ቅብጢው፡ብሳቱ፡ጳውሎ፡— ባማርኛ፡ኪኑሎ፡
ምንስ፡ዐይናማ፡ቢለው፡— ዐይን፡ወጼት፡አለው፡
ዐረም፡የዋጠው፡ኛቁር፡ጤፍ፡— የብሳቱ፡መጽሐፍ፡
ዘሩ፡ቡቃያው፡ሐንፌጽ፡— የትግሬ፡መሬት፡ሠርጽ፤
ሐንሬጽም፡ማለት፡ክልስ፡— ወይም፡ስንዴና፡ገብስ።
ኹሉን፡እንደ፡ርሱ፡በርሱ፡ሐግ፡— ዕውር፡ዐንካሳ፡ለማድረግ፡
ሐጉም፡፩፡ባሕርይ፡፩፡ግብር፡— ወልድ፡ቅብ፡ማለት፡፫፡ነገር፤
በደንባሬው፡ሕዝብ፡አእምሮ፡— ይህ፡፫፡ቃጭል፡ተጨምሮ፡
ሦስት፡መለኮት፡እያሰኘ፡— ስንቱን፡አካል፡አሞኘ።
አንዱን፡መለኮት፡በማመኙ፡— የ፫፡አካል፡ግብር፡ለማቅለኙ፡
ባንዱ፡አካለ፡ወልድ፡ከሚስቱ፡— ማነው፡የማይስት፡በኹለቱ፤
አይለቅምና፡ሳያቀስ፡— ያዘቈነ፡ጳጳስ፤
ጳጳሱም፡ሣልስ፡ሰላማ፡— ድቅድቅ፡የቀን፡ጨለማ፤
ወይም፡ሬያታይ፡ዘፀጋም፡— የቀያፉ፡ወንድም።
የወንጌል፡ተረት፡አማምሳይ፡— በማን፡ደረሰ፡በኛ፡ላይ፤
ዕውር፡ዕውርን፡ቢከተል፡— ተያይዞ፡ገደል።
ዐንካሳውንስ፡ዐንካሳው፡— በምን፡ቁሞ፡ያንሣው።
አቡን፡የሾመው፡አስነባቢ፡— እየመለሰኸ፡ካቡን፡ግቢ፡
ገበታዋሬያ፡ስታነብ፡— እንዴት፡አትጠበብ፤
ሐሳዊ፡መሲሕ፡ማለት፡— ቀንድን፡አለወይ፡ኹራት፤
በምን፡ይለያል፡ከይሁዲ፡— የክርስቲያን፡ከሐዲ።
የሉስን፡መሲሕ፡የማይል፡— ርሱ፡እንደኾነ፡ስማ፡አስተውል።
ስላልታነጹ፡እንደ፡ጽርሐ፡— በሐዋርያት፡ከኰኵሐ፡
ወልድን፡ቅብ፡ብለው፡አቡኑ፡— እንደ፡ገበሬ፡ካመኑ፡
የተሰብአን፡ምርት፡ተቀብዐን፡— በምን፡ያፍሡት፡ይኾን፤
የነቢያትስ፡አዝመራ፡— አለመሲሕ፡ጐተራ፡

www.ethiopianorthodox.org

፻፸፰

ያ፡ ኹሉ፡ ንባብ፡ ከምር፡ ቃል፡ — በምን፡ ይከተታል።
ምነው፡ ትምርቱ፡ ቢቀድም፡ — ሐር፡ ከመጠምጠም፤
ትምርትስ፡ ቀድሞ፡ ነበር፡ — በማርቆስ፡ ወንበር፡
ዲሬኑት፡ እንጂ፡ ተንባላት፡ — በጋሻቸው፡ ዕንብርት፤
ጋሻቸውም፡ ቱርክ፡ ዐረብ፡ ነው፡ — ቍርአን፡ የሰጐደው፡
ወይም፡ ሰሌዳ፡ የላም፡ ቍርሬ፡ — ኅነሬና፡ ሸነሬ።
የጐዲት፡ ግኝም፡ የግራኝ፡ — ባለኹለት፡ ስንኝ፡
ቴዎድሮስና፡ ዮሐንስ፡ — ሄሮድስ፡ ወጲላጦስ፡
በነገሡበት፡ ወራት፡ — ተለወጠች፡ ትምርት።
በሰላማ፡ ዕብሬት፡ ጻድቃን፡ ኹሉ፡ — እንደ፡ ኢየሱስ፡ ሲሰቀሉ፡
ሃይማኖት፡ ፀሐይ፡ ብትጨልም፡ — ምግባር፡ ጨረቃም፡ ኾነች፡ ደም፤
ሕዝቡም፡ ታወከ፡ ካርብ፡ እስካርብ፡ — ጢስ፡ እንደ፡ ገባው፡ ንብ፡
ስለ፡ ሃይማኖት፡ ሰው፡ መግደል፡ — መሥዕት፡ ማቅረብ፡ እስኪመስል።
ፍጹም፡ ቍጥራቸው፡ በሕዝብ፡ ውስጥ፡ — ከ፳፱፡ የሚበልጥ፡
ካህናቱ፡ እጨጌው፡ አቡኑ፡ — መለካውያን፡ ስለ፡ ኾኑ፡
የቅባቶች፡ ሦስት፡ ዐይነት፡ — የካሮቹም፡ ዐምስት፥
ስምንቱ፡ ባህሎች፡ እኒህ፡ ኹሉ፡ — ሰው፡ ግደሉ፡ ይላሉ።
ዐይኑ፡ የጠፋ፡ ፊትል፡ — ይህ፡ ፲፡ ልቅ፡ ባሕል፡
ከናባ፡ አውጣኪ፡ ውጥንቅጥ፡ — ከዚያ፡ ከመጥሮ፡ ጥጥ፡
የተፈተለ፡ በመላ፡ — ሰላላና፡ መላላ፡
ጥጡም፡ ፈታዩም፡ ሸካራ፡ — ፈትልነቱም፡ የግራ።
እንዝርቱም፡ አቡን፡ መፍትያው፡ — መጽሐፍ፡ የሚፍቀው፡
ራሱ፡ የወርቅ፡ የብር፡ — ዘንጉም፡ ያልጋ፡ ሸንኰር፥
በሊቃውንት፡ እጅ፡ ሲነዘር፡ — የማይሸከረከር።
ቋንጣውም፡ አምጀር፡ ደረቅ፡ ሥጋ፡ — ምላሱ፡ እንደ፡ ሾከ፡ የሚዋጋ፤
ወይም፡ ራሱ፡ በኵቦ፡ — የተቀለሰ፡ ሽቦ፡
ማሩን፡ አምርሮ፡ ሲናገር፡ — ወተቱንም፡ ሲያጠቍር፡
ከንብም፡ ኾነ፡ ከላም፡ — ወቃሽ፡ ነቃሽ፡ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፯

አላምጀርና፡ አላቡን፡ — ማነው፡ ሬታያችን።
የፌትሉን፡ ነውር፡ የሚያወጣ፡ — ጠቢብ፡ ሸማኔ፡ ስለ፡ ታጣ፡
ምንም፡ ቢሠራው፡ ንጉሡ፡ — ይህንን፡ የጳጳስ፡ ልብስ፡
እንለብሰውም፡ ባዋጅ፡ — እንሞተዋለን፡ እንጅ፡ (፩)
እንዲህ፡ እያሉ፡ የታረዱ፡ — ወይም፡ የተሰደዱ፡
ከናግራን፡ ሕዝብ፡ አያንሱም፡ — በሰማዕታት፡ ስም፤
ኻያ፡ ሺ፡ እንጂ፡ ነው፡ በግእዝ፡ — የናግራን፡ አኃዝ።
ሰማኒያ፡ እንዲባል፡ ስምንት፡ — ዜሮ፡ ሲገባበት፡
ዜሮም፡ በዜሮው፡ ሲታከል፡ — ፰፻፡ እንዲባል፡
ዛሬም፡ ካንድ፡ ቤት፡ ወጥቶ፡ — ዐሥርን፡ ዐልፎ፡ ወደ፡ መቶ፤
ለዚህም፡ አለኝ፡ ምስክር፡ — የማይጠረጠር።

መወድስ፡ ዘኦርቶዶክሳዊ፡ ክፍለ፡ ዮሐንስ።

ሃይማኖተ፡ ቄርሎስ፡ ኮነት፡ ግማዴተ፡ አብድ፡
ወኍልቈ፡ ተመትሮ፡ አብዝኃት፡ ኀበ፡ ኢሀሎ፡ ንጉሠ፡
ካህነ፡ ደብረ፡ ኤፍሬም፡ ቅድመ፡ እምዘመተራ፡ ነአስ፤
ወአመ፡ ኢዮርብዓም፡ ለምስሌ፡
በእዴ፡ ነቢይ፡ ዘተሠጠት፡ ልብስ፡
እንተ፡ እምኵሉሰ፡ ያጠይስ፡
ወዘያነድድ፡ ለቡና፡ ኢትበሊ፡ ኢደምያስ፡
ተቀብዐ፡ ቅብዐ፡ ውሳጤ፡ ሕሩመ፡ ተውሳኮ፡ ክርስቶስ፤
ወአኮ፡ በተቀብዖቱ፡ በኵሬ፡ ውሉዱ፡ ለዮርዳኖስ።
ወእንዚ፡ ትትናገሪ፡ ዘንተ፡ በአድንኖ፡ ክሣድ፡ ወርእስ፡
ከመ፡ አነ፡ ሰማዕኩኪ፡ ኢይሰማዕኪ፡ ጳውሎስ።

ከዘፋኝ፡ ዳዊት፡ ከቴዎድሮ፡ — እስከ፡ ምኒልክ፡ ዐምባ፡ ጊሮ፡
በናባ፡ በዝብዝ፡ ግርግርታ፡ — ጐንደር፡ ሙቶ፡ እስኪሬታ፡
አላየኸምይ፡ ትንቢቱን፡ — ለምንት፡ አንገለጉን፤
የስንዴው፡ መሲሕ፡ አዝመራ፡ — ብዙ፡ ሊቃውንት፡ ስላፈራ፡
ጳርሶ፡ ሲታጨድ፡ እንደ፡ ገብስ፡ — የሰው፡ ራስ፡ ምላስ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፻፺፰

የመጻሕፍትን፡ጠባይ፡— ምነው፡አጥርተህ፡የማታይ፤
ተመርጓል፡ይኾን፡በጭቃ፡— ያይነ፡ልብኽ፡ጨረቃ።
ዕውር፡ጠንባሳ፡በሚያሰኝ፡— ባውጣኪ፡ኩፋኝ፡
ምንም፡ዐይንኽ፡ግብጽ፡ቢበልዝ፡— ጥሩ፡ነው፡ቋንቋኽ፡ግእዝ፡
ከያፌት፡ቋንቋ፡ከሴም፡— እጅግ፡ድምፀ፡መልካም።
ልቡን፡ፈጽሞ፡ስላልሰጠ፡— ግእዝ፡አቶ፡በለጠ፡
ዥርባ፡ዘርባውን፡እያከኩ፡— ልጆች፡መጽሐፍ፡አወኩ፤
ላይ፡ላዩን፡ማከክ፡ቀርቶበት፡— ምነው፡በጠቈሙት።
ሐዲሱን፡ጥራዝ፡ከነሊቁ፡— እንዴ፡ቅኔ፡ሲነጥቁ፡
ዐካኪ፡ዘራፍ፡እያሉ፡— ዛሬም፡ይዴነፋሉ፤
ከኛም፡እንሆ፡መወድስ፡— የድንፋታቸው፡መልስ።

ተወልድ፡ዕሉት፡ትውልዴ፡አውጣኪ፡
እንተ፡በዐመፃ፡ወለደት፡ጉባኤ፡እንበለ፡አብ፡
ትእምርተ፡ትርጓሜ፡ተኅሠሡ፡ወኢይትወሀባ፡ንባብ፤
እክለ፡ዐማኑኤል፡ሰማርያ፡
ወንጌል፡ዘይሴሰይዋ፡አሕዛብ፡ወሕዝብ፡
እስመ፡ኪያሃ፡ኢይጸግብ፤
ወኢያረውዩ፡ጳውሎስ፡እንተ፡ኤሬሶን፡ሐሊብ።
ትሁቦሙኒ፡ለውሉዱ፡ዘኢይትወሀብ፡
አርዌ፡ምድር፡ህየንተ፡ዓሣ፡ወህየንተ፡ኅብዝት፡እብነ፡አዚብ፤
እስመ፡እምኔሃ፡ተንሥአ፡ክህነተ፡አበው፡ጥበብ፤
ወተሀይደ፡እምኔሃ፡አእምሮ፡መንግሥተ፡ልብ።

ክፍል፡ራብዕ።

በእንተ፡ባሕርያት፡ወግብራት፡ወተዋቅቦቶን፡እምሕሳታት።
ወልዴታትኒ፡ባሕርያውያት፡ይሰመይ፡ግብራት፡ለገባሪሆን፡አካል።

የባሕርይ፡የግብር፡ምንታዌ፡— በምስጢረ፡ሠጋዌ፡
አያለያይም፡ነበር፡— ያንዱን፡አካል፡ማኅበር።
የሚያለያይስ፡የሚያጣላ፡— የናባ፡ሆይ፡ዲቃላ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩፡ አካል፡ ብሎ፡ ፪፡ ሠሪ፡— ወይም፡ ፩፡ ግብር፡ ፩፡ ባሕሪ።
ባንድ፡ አካል፡ በረቱ፡ ባንድ፡ አኳራ፡— ፪፡ ሠሪና፡ ፪፡ አውራ፡
አይስማማውም፡ ይህ፡ ተረት፡— ለወልድ፡ ዋሕድነት።
የሥጋን፡ ሥራ፡ በሠራው፡— ቃል፡ ሥጋ፡ ኹኖ፡ ካልሠራው፡
አምላክ፡ ወሰብእ፡ ካልተባለ፡— እንደ፡ ምን፡ ሞተ፡ ተሰቀለ፤
ኹለት፡ ሠሪና፡ አንድ፡ ባሕርይ፡— የሥጋው፡ ቃል፡ ተጣይ።
፪ቱም፡ ዐይነት፡ ኑፋቄ፡— መርዝ፡ ያለበት፡ ዐረቄ፥
ጥኑውን፡ ትምርት፡ የሚያገኝሽ፡— ናሳ፡ የሚያበሳሽ፤
ማነው፡ ቤት፡ ክሊያን፡ በጥባጭ፡— ይህን፡ የሚገነጭ።
በየሱስ፡ ትምርት፡ ታምራት፡— ዐይኑ፡ ካልበራለት፡
ምንስ፡ ዐይኖቹን፡ ቢያፈጥ፡— እኛን፡ ሊገላምጥ፡
የተዋሕዶን፡ ጎዳና፡— ዕውር፡ መቼ፡ ያየውና።
፪፡ ባሕርይም፡ ሊኼድ፡— በ፪፡ ልዩ፡ መንገድ፡
ከመናፍቃን፡ ወንበዴች፡— እንዳገኘው፡ አንዳች፡
ሑሰት፡ ውሳጤም፡ አራዊት፡— እንዳይቃወሙት፡
ኃሻውን፡ አካል፡ አንግቦ፡— ይመራዋል፡ ተዓቅቦ።
ተዓቅቦም፡ ማለት፡ ባንዱ፡ አካል፡— እንደ፡ ሠምና፡ እንደ፡ ፈትል፡
የባሕርይና፡ የግብር፡— ተጣባብቆ፡ መኖር።
አካልም፡ የወል፡ ማኽለኛ፡— እንደ፡ ምሰሶ፡ እንደ፡ ዳኛ፡
ያስተባብራል፡ ኹለቱን፡— ባንድነቱ፡ ብርሃን።
ምንም፡ ግብርና፡ ባሕርይ፡— ተጣባብቀው፡ ብናይ።
አለቋሚ፡ አካል፡ ባለቤቱ፡— ከቶ፡ አይነድም፡ እሳቱ።
የባሕርይ፡ የግብር፡ ጠቅላይ፡— አንቀጽና፡ ስም፡ ተቀባይ፡
ወልድ፡ ዋሕድ፡ ወበኵር፡ ስመ፡ መንታ፡— ምሰሶና፡ ገበታ፡
አዳራሻችን፡ ሃይማኖት፡— የተዋቀረበት።
አምላክና፡ ሰው፡ አንድ፡ አካል፡— ኹለት፡ የማይባል።
በሰውነቱ፡ የሰው፡ ልጅ፡— የሱስ፡ የአብ፡ ቀኝ፡ እጅ፡
ባምላክነቱም፡ ነባር፡— ዓለም፡ ሳይፈጠር፤

www.ethiopianorthodox.org

እንዘ፡ ያነሉሀጺ፡ ነቢየ፡ እምቤተ፡ እንበረም፡ ወሐዲ፡
ድኅረ፥ ሰነቢዩ፡ ኄኖክ፡ ገዲመ፡ ነበልባል፡ ወሰዲ፥
መሳእክተ፡ ርቀት፥ ወግዘፍ፡
እለ፡ ይትዓየኑ፥ ዐማኑኤል፥ ዐውዲ፡
እምቅድመ፡ ትድምርት፡ ወተዋሕዲ፡
ኦምጣነ፡ አኮ፡ ዘኮነ፡ እግዚአብሔር፡ ሐዩዲ።
በእሳቱ፥ ለሰልና፡ ኡኅ፥ ለሠከ፥ ኅጢአት፡ አንደዪ፤
ወበትሕትና፡ እም፡ ተዋረደ፥ እንዘ፡ ኢያጺዕሌ፡ ተዋርደ።
እመኔ፡ ክልኤቱ፥ ወለዶ፥ ሕፃነ፥ አሐዶ፥ ተዘምደ፡
በዘወለደ፡ ኢወለዴቶ፡ ወበዘወለዴቶ፡ ኢወለደ።

ክፍል፡ ኃምስ።

በእንቱ፡ ሠለስ፥ ልደት፡ ማኅቶቱ፡ ኃምስ፡ ክፍላት፡ እለ፡ ነሉሀእ፡ ቅኑበዐ፡ ምስሌሆን፥ በገጣዕይሆን።

፩ኛው፡ ልደት፥ ዳግም፡ ሐጫ፡ — ዳግማይ፡ አዳም፡ የሚያደርጋ፤
በሊቃውንት፡ አፍ፡ ሲነገር፡ — ምንም፡ ከተማው፥ ቢሸበር፡
በኍረ፥ ልደት፡ ነው፡ ለፍጥረቱ፡ — በሦስተኛ፡ ልደቱ።
፪ኛ፥ ልደት፡ ከሌለው፡ — እንዴት፡ ዋሕዱን፡ በኍር፡ አለው፤
ታናሽ፡ ሳይኖረው፥ ትከታይ፡ — ካባት፡ ከናት፡ ባሕርይ፡
ለ፩ዱ፡ ቅንጣት፡ ለጅ፡ ብኵርና፡ — አይስማማውምና።
፫ኛ፡ ልደት፡ የግብር፡ — ወይም፡ የጸጋ፡ ምስጢር፤
ግብርና፥ ጸጋም፥ አንድ፡ ወገን፡ — የወሳዴው፥ ማሕፀን፡
ኋላ፥ እስኪሌታ፥ በጉባኤ፥ — ማኅተሙ፡ ትንሣኤ።
የግብሩ፡ ልደት፡ ከባሕርይ፡ — ተለዴቶ፡ እንዲታይ፥
ለምዐኒ፡ ብዬ፡ ልምራት፡ — የልደቱን፥ ሠለስት፥
ሰላሙም፥ አይቀር፥ ይመጣል፥ — ተሣሀልከ፥ ሲባል።
በቤት፥ ልሔም፡ አውራጃ፡ — እየሬነጩ፡ እንዴ፡ ጥጃ፡
የሰማይ፡ ጭፍሮች፡ ሲሸልሉ፥ — ወሰላም፥ በምድር፡ እንዲሉ፤
ሠለስት፥ ወሰላም፡ ነውና፡ — መጨረሻው፡ ምስጋና።

www.ethiopianorthodox.org

፩፻፬

እንደ፡ሰማይ፡ቀስቱ፡እንደሳማ፡— ፫፡ዐይነት፡ባለው፡በ፫፡ዜማ፡
በግእዝ፡በዕዝል፡ባራራይ፡— ተወሳዲውን፡ሳይለያይ፡
የዜማው፡መምር፡አብ፡ራሱ፡— እያስጮኸኒ፡በመንፈሱ፡
ወልድየ፡አንተን፡ስናዜም፡— ዮም፡ወለድኩከን፡መድገም፤
፫ኛው፡ልደት፡ይህ፡ስለቻ፡— የኹለቱ፡መክተቻ።
ማስረያውም፡ጥብቅ፡በኵርነት፡— ሌሎች፡የማይፈቱት፤
እንፍታም፡ብለው፡ቢከጅሉ፡— ቀርበው፡ሊፈቱት፡የማይችሉ፤
እንደ፡ፈርዖን፡ሕልም፡አስቸጋሪ፡— ሳባይ፡ጠንቋይ፡ለመሠሪ።
የፈርዖንን፡ሕልም፡የፈታው፡— አለዮሴፍ፡ማነው፤
የሲናውንም፡ራእይ፡— አለድዳው፡ነቢይ፤
ያልተጣፈውን፡ከሚያነብ፡— ከዚያ፡ከሳታፍ፡ሕዝብ፡
ያየው፡ሰው፡የለም፡ንባቡን፡— ስንኳን፡ትርጓሜውን።
ለባቢሎን፡ንጉሡ፡— አለዳንኤል፡መንፈሱ፡
የጠፋውን፡ሕልም፡አግኝቶ፡— ማን፡ነገረው፡አፍታቶ።
ቀድሞ፡በፈርዖን፡ዘመን፡— ኋላም፡በባቢሎን፡
ከ፫ቱ፡ይልቅ፡የከበሩ፡— ብዙ፡ሰዎች፡ነበሩ፤
የተናቁትን፡መምሬን፡— የግዜር፡ንዋየ፡ውስጥ፥
ከነኢልያብ፡ከነሳባ፡— ዳዊትን፡መርጦ፡እንደ፡ቀባ።
ምስጢርም፡ቢገልጥ፡ሳልባሌ፡— መቼ፡ለናቦ፡እገሌ፤
እናቦ፡እገሌስ፡ይቀመጡ፡— እኛን፡እያጐመጡ።
ጥጃ፡ቢሳሳት፡ከናቱ፡— ነገር፡ቢሳሳት፡ከጥንቱ፥
እንደ፡ዳኛው፡የግዜር፡ቃል፡— የጥንት፡ይብቃ፡የሚል፤
ምንም፡ይህ፡ዓለም፡ጠማማ፡— የዳኛ፡ቃል፡ባይሰማ።
በሠባው፡ቃሉ፡በየሱስ፡— ዓለሙን፡ሊያድን፡ሊፈውስ፡
ወልድየ፡አንተ፡ያለውን፡— ወልደ፡ማርያምን፡
አብ፡በመንፈሱ፡ቀብቶ፡ሹሞ፡— ዮም፡ወለድኩከ፡ካለው፡ደግሞ፡
ማመን፡ይገባል፡እንደ፡ጥንት፡— በሠስተኛው፡ልደት።
ሠለስቱ፡ዱቂቅ፡ልደቶች፡— ያ፭፡ወልደ፡አምላክ፡ገንዘቦች፡

www.ethiopianorthodox.org

ያተረፉቸው፡ወጥቶ፡ወርዱ፡— ከኛም፡ጎራ፡ነግዴ፤
ተባብረውና፡ተጫፍረው፡— ሦስቱም፡አሉ፡ያኸው።
ወሃቤ፡ጸጋ፡ዘእምጸጋ፡— ሲዋሐድ፡ሲለብስ፡የኛን፡ሥጋ፡
መሲሕነቱ፡ከዋም፡— ተስማምቶለት፡በጣም፡
ቀዳሚ፡ጸጋ፡መኾኑን፡— ወለድኩከ፡አስረዳን።

እኛም፡ከታዲያምን፡በዋም፡ሕጉ፡— ለወለድኩከ፡ሰርጉ፡
ሥጋውን፡ደሙን፡ጨምረን፡— በሥሉስ፡እንብላው፡ልደቱን፤
መድኃኒትነት፡ከብኵርና፡— ኹሉም፡አሉበትና።

በሰውነቱ፡ሥጋው፡ቃል፡— ለአብ፡ምኑ፡ነው፡ብትል፡
ግብሩ፡መሲሑ፡ካህኑ፡— በኵረ፡ምዕመናኑ።

የቅዱስ፡ወንጌል፡አርእስት፡— ወልደ፡አብርሃም፡ወልደ፡ዳዊት፡
ሣክ፡ያቀዳጃት፡ዲቀ፡ጽርሐ፡— የመሲሕ፡ልጅ፡መሲሕ።

ካህንም፡ኩኖ፡ስለ፡ሕዝቡ፡— መሥዋዕት፡ጸሎት፡በማቅረቡ፡
አስታራቂና፡አማላጅ፡— ወይም፡ነገረ፡ፈጅ፡
ለሰማይ፡ርስት፡የሚያበቃ፡— አለቃና፡ጠበቃ።

የአብርሃም፡ቤት፡እንግዲ፡— ዋም፡ወለድኩከን፡ሲያሰናዲ፡
በይሥሐቅ፡ልደት፡አየማለ፡— ዓመ፡ከመ፡ዋም፡ሰላለ፡
በሰው፡ልጅነት፡አመካኝቶ፡— ዋምን፡ሲበላ፡ዐንጉቶ፡
ቂርሎስ፡ነው፡አሬ፡ወርቅ፡— ማነው፡ያላየው፡ሊቅ።
ዋም፡ወለድኩከን፡በቅባት፡— አብ፡ካልጨመረበት፡
የሰው፡ልጅነት፡ብቻውን፡— አያኰራም፡ሰውን።
ከንዲት፡በቀር፡ብልጽግና፡— ለሰው፡የለውምና።

ወለድኩከ፡ግን፡የአብ፡ዘውግ፡— ኹሉን፡ሲጠራ፡ወደ፡ሠርግ፡
ወልድን፡አይለይም፡ከናቱ፡— ስንኳን፡ከሠራዊቱ፤
ጉባኤ፡ቃና፡ዘገሊላ፡— እንዲህ፡ተብሎ፡ይፈታላ።

ሠራዊቶቹም፡ወንድሞቹ፡— ኹሉም፡የአብ፡ልጆቹ፤
ድኺቱ፡እናቱ፡ማርያም፡— ስለ፡ለመነች፡በአብ፡ስም፡
ጥኑውን፡ውሃ፡ወይን፡አድርጎ፡— ያጠጣቸው፡እንደ፡ርጎ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፻፴

ዳዊት፡ሰሎሞን፡የሚባሉ፡— ኹለት፡አዝማሮች፡ሊሊ፡ሲሉ፡
ሦስተኛ፡ዳግሞ፡ልትዘፍን፡— ከመካከላቸን፡
እናቱ፡እትዬ፡ተነሣች፡— ልጅ፡ወንድሜ፡እያለች።
የዑምን፡ቃና፡ሲያጣኝም፡— በሎጕ፡ልጆች፡ጌሠም፡
ልደታቸውን፡ጐንደር፡ባታ፡— መባቻ፡አድርጎ፡ለሎጕ፡ጌታ፡
እንዲህ፡እንዲለ፡ጐንደሬው፡— በሚ፡በዝኁ፡ቅኔው።
በዘርዐ፡አቡሆን፡ኮና፡እኄቱ፡ውሉዶን፡እኄት፡
ኣመ፡ወርኃ፡ሐጸጽ፡ወንትጋ፤
ለከሰ፡አምላክ፡ክርስቶስ፡ቀዳሜ፡ጸጋ፡
ወለተ፡ሐና፡ጠባብ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡እኄትከ፡
እንዘ፡እምከ፡በሥጋ።
በዋዜማውም፡ቀጠሉ፡— እንዲህ፡እንዲለ፡ኣባ፡ተስፉ፡
በሠሌሳዊ፡ልደት፡እምአቡሁ፡
ሀሉወነ፡ተዘምዱ፡ምስሌሁ።
ከሦስተኛው፡ልደት፡ጫፍ፡— ኹለተኛ፡ሲቀኛፍ፡
ርግብ፡ውእቱ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ለዘመዱ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
በወልድ፡አካኪድ፡በአብ፡ጕዞ፡— ከመንፈስ፡ቅዱስ፡አያይዞ፡
ዑም፡ያነገሠት፡በንባብ፡— ልደቱ፡እቴጌ፡ምንትዋብ፡
ሱብሉ፡ወንጌልም፡ይሏቷል፡— ሊቃውንተ፡ወንጌል፡
ዐሸተው፡ሊልፍለው፡የበሉት፡— የምስጢሯን፡እሸት።
ጣይቱም፡የሚል፡አይታጣ፡— ሦስተኛ፡ስም፡ሲያወጣ፤
ከጣይቱም፡ሌት፡በጐንደር፡— መነን፡ይሏት፡ነበር፤
አኹንም፡መነን፡እንበላት፡— እንደ፡ኛንቱ፡ሠርዐት።
የክህነቱና፡የመንግሥቱ፡— ርሷ፡እንጂ፡ናት፡ዘውዲቱ፤
ቀድሞ፡የደሉት፡አዳም፡— ሲቀባ፡ሲሾም፡ሲሸለም።
የአዳም፡ልጆች፡ሊቃውንት፡— ዳግማይ፡አዳም፡ያሉት፡
የቤተ፡ዳዊት፡አቢስሎ፡— ዐልጋ፡ወራሽ፡ተብሎ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለሔዋን፡አክሊል፡ባዲም፡ዘውድ፡— ተቀብሎ፡ሲነግሡ፡ለአይሁድ፡
ምኒልክ፡ይኹን፡ምኒልክ፡— ወዲ፡ዘውዲቱ፡አምላክ፤
የለውምና፡የሚበቃ፡— የሰብአ፡ሰገል፡ዕቃ፡
ኃይለ፡መለኮት፡የገዘው፡— ከሣህለ፡ሥላሴው፡
(ማብ፩፫—፩፪። ኢሳ፷፡፮፡፲)።
ዐቃቢ፡ሰዓት፡ከብቴም፡— በሥላሴ፡ማኝም፡
አለማየትን፡ይሰብካሉ፡— ዐይናሞቹ፡ነን፡ለሚሉ።
መንግሥተ፡ሰማይ፡
ኀቤሁ፡ለጴጥሮስ፡እንዘ፡ቅርብት፡
ኢነጸረ፡ጴጥሮስ፡መልክአ፡ተሠዕሎተ፡መልክአ፡ብርሃን፡
እስመ፡ተፈጸመ፡በታቦር፡ማኅፀን።
ከመሰ፡ኢንበል፡ይእዜ፡እመ፡ይቀርብ፡መካን፡
ነጽሮ፡ቅሩብ፡ኢይሰእን፤
ቀራንብት፡ኀቤሁ፡ለዐይን፡እንዘ፡ቅሩን፡
ቀራንብተ፡ኢይኔጽር፡ዐይን።
ካይሁድ፡ጉባኤም፡እያስጠጉ፡— መናፍቃንን፡ሲወጉ፡
ሠለስቱ፡ምእት፡ሰብአ፡ኒሴ፡— እንዲህ፡እንዳሉ፡በቅዳሴ።
ኦ፡ዘአሜሃ፡ትውልድ፡ፃሬ፡አዕይንቲሆሙ፡ከመ፡ኢይርአዩዋ፤
ደንቀዋ፡እዘኒሆሙ፡ከመ፡ኢይስምዕዋ፤ ወተጸለለ፡ልቦሙ፡ከመ፡
ኢያእምርዋ፡ለሠልስ፡ልደት፡ወበዓለ፡ልደት። ይእቲኬ፡መድኃኒት፡
አክሊለ፡ክህነት፡ወመንግሥት፡እንተ፡ኀሠሠዋ፡ወያድዋ፡ነቢያት፤
በከመ፡ጽሑፍ።

## ክፍል፡ሳድስ።

በእንተ፡ፅንሳ፡ወፍሬ፡ከርሣ፡ለዮም፡ዕለት፡ዳግማይ፡አዳም፡
ዘብዙኃ፡ሐሳብ፡ሁጣ፡ወንዋየ፡ውስጣ።
ብሉዩ፡ክረምት፡አልፎልን፡— በሐዲሱ፡ዘመን፡
መስከረማችን፡ዮም፡ሲጠባ፡— ልደት፡ዐዲሳበባ፤
ዐዲሳበባም፡ኘምቀት፡— ብዙ፡ፍሬ፡ያላት።

www.ethiopianorthodox.org

፪፻፷፮

በንባብ፡ ውጠው፡ ሰብአ፡ ሮሚ፡ — ምንም፡ ቢተፉት፡ በትርጓሜ፡
ማነው፡ ያስረዳን፡ አለዮም፡ — የበኵርነቱን፡ ጣዕም።
የዮምን፡ ገንዘብ፡ በደብተሬ፡ — ዘርዝሬና፡ ደምሬ፡
ደግሞ፡ አሳያለኹ፡ ለሬታሽ፡ — እንዲሰጠኝ፡ ምላሽ፤
ወደም፡ ድምሩ፡ በመሰንቆ፡ — ልክ፡ መኾኑን፡ ዐውቆ፡
ደስ፡ ፌቅ፡ እያለው፡ እንዲያነብ፡ — የልደትን፡ ሒሳብ።
መዋዕለ፡ ፅንስ፡ ዘጠኝ፡ ወር፡ — ዐሥር፡ ተብሎ፡ ሲቈጠር፡
ፅንስም፡ በልደት፡ ሲፈጸም፡ — እንዲጠቀለል፡ በዮም፡
የወለድኩኩም፡ ሩባዔ፡ — ከፅንስ፡ እስከ፡ ትንሣኤ።
ከፅንሱ፡ ጸደል፡ ካረቦን፡ — እስከ፡ ትንሣኤው፡ ብርሃን፡
ሠላሳ፡ አራቱ፡ ዓመት፡ — አንድ፡ ዮም፡ አንድ፡ ዕለት።
ያረቦን፡ ልደት፡ ድርሰ፡ ቍርጥ፡ — መርቀቅ፡ መታደስ፡ መለወጥ፤
የተወለደ፡ ከመንፈስ፡ — መንፈስ፡ ነውና፡ ሲታደስ።
የትንሣኤው፡ ለት፡ እሑድ፡ ቀን፡ — ወንድሞቼ፡ ሲል፡ አርድእቱን፡
አያሳደሞይ፡ ይህ፡ ትርጓሜ፡ — ያረቦኑን፡ ፍጻሜ፤
ትንሣኤ፡ እንጂ፡ ነው፡ ባለዮም፡ — የልደቱ፡ ማኅተም።
ጉባኤ፡ ቃና፡ ልደቱ፡ — አብ፡ የቈጠረለቱ።
እንደናቱ፡ ጡት፡ ፪፡ ቤት፡ — በሐሳበ፡ ዳዊት።
በማሕፀን፡ በጎል፡ በጎልጎታ፡ — በሠግው፡ ቃል፡ መኝታ፡
፩ኛውና፡ ፫ኛው፡ — ፪ኛውን፡ አማክለው፡
ወልድየ፡ አንተ፡ በራስጌ፡ — ዮም፡ ወለድኩከ፡ በግርጌ፡
እንደ፡ ኹለቱ፡ መላእክት፡ — ኹለቱም፡ ገልተው፡ ታዩለት።
መፀነሱና፡ መቀበሩ፡ — ስለ፡ ተነጻጸሩ፡
ትንሣኤን፡ ልደት፡ እንደለው፡ — ግብረ፡ ሐዋርያው፡
ሐዋርያውም፡ ጳውሎስ፡ — ዮምን፡ መሳልሶ፡ የሚጠቅስ፤
ሌላውንማ፡ ድርሳን፡ — ስንቱን፡ እንጠቅሳለን።
ዮምንም፡ ብቻ፡ ለሚሬቱ፡ — በኻያ፡ ዘጠኝ፡ መጋቢት፡
ደግሶ፡ አቅርቧል፡ ስንክሳር፡ — የኹለቱን፡ ተዝካር።

www.ethiopianorthodox.org

የበትረ፡እሴይ፡አበባ፡— ዕትብት፣እንደ፡ጡት፡ሲጠባ፡
ፅንሱን፡ልደቱን፡ሊቀሠሙ፡— እየተቀዳደሙ፣
ሰባቱ፡ንቦች፡ሀብታት፣— ስለ፡ሰፈሩበት፡
ዮም፡ወለድኩከም፡ጽጌ፡ረዳ፣— ከአብ፡ስለ፡ፈነዳ፡
ከመጋቢት፡ጧት፡እስከ፡ማታ፡— ብዙ፡ልጅ፡ወንድም፡ሰጥታ፡
የትማልሙን፡ወልድ፡ዋሕድ፣— በኵር፣አሠኘችው፡ዮም፡ወሳድ፤
በበኵርነቱም፡ፍጹም፡— ባለብዙ፡ወንድም።

ዋሾቼ፣እንደኾን፣በነገሬ፣— ቄርሎስ፡ሳይቀር፣ምስክሬ፡
ዲኖው፡ጳውሎስ፡ይጠየቅ፡— እማኜም፡ሊቁ፡አሬ፡ወርቅ፡
ዮምን፣አግብቶ፡የፈታት፣— በነዳዊት፣ሠርዐት፡
መምሬ፡ዋሴም፡ነባሪው፡— ሃይማኖተ፡አበው፣
ዮምን፡ሲያፋታ፡ሲያገባ፡— ቃሉ፡የማይዛባ።
አሬ፡ወርቅንም፣ቄርሎስ፤— እንዲህ፡ብሎታል፡በመንፈስ፡
በኹለተኛው፣ድርሳንኽ፡— እግዜር፡ስላዘዘህ፡
የፈታኻትን፡ዮም፣ከበድ፣— እኔም፣ከርሷ፡እንድወልድ፡
በእስትጉቡእ፡ድርሳኔ፡— እባክኽ፣ላግባት፣እኔ።

የምወልደውም፡ከዮም፡— ቅዱስና፡ፍጹም፤
የመጽሐፍ፡ስሙ፡አባ፡ተክሌ፣— ሃይማኖት፡ዲንጋሌ፡
አንተንና፡እኔን፡የሚመስል፡— በመልክና፡በባህል፤
ከሐራጥቃም፣ሲዋጋ፡— የሚያሠጋ፡እንጂ፡የማይሠጋ።

ላንዱ፣ሠባው፡ልጅ፡ካንድ፡አባት፡— እንዲህ፣በባሕርይ፡በቅባት፡
ወልድ፡ዋሕድ፡ወበኵር፡የሚያሰኝ፡— ኹለት፡ልደት፡ሲገኝ፤
በወንጌሉ፣አሠር፡በጥርጊያው፡— በማያሳስተው፣
ቃል፡ሠጋ፡ኾነን፡ተከትላ፡— ሳታፈገፍግ፣ወደ፡ኋላ፡
እንደ፡ዮሐንስ፡ወንጌል፡— ምሉእ፡ጸጋ፡ብትል፣
ደብረ፡ሊባኖስ፡እናትኽ፡— የተሳሳተች፡መስሎኽ፣
ለምን፡ታማለኽ፡አባ፡ሆይ፡— ተዋሕዶ፣መሳይ።

ዐራጆች፣ደሮን፣ሲደሉ፡— በመጫኛ፡እንዲጥሉ፣

www.ethiopianorthodox.org

፱፻፲፯

ክፍል፡ ሳብዕ፡ ፍጹመ፡ መልክአ፡ ወስም።

መልካ፡ መድኀኒ ያለም፡ በሃይማኖት፡ ቁሞ፡ መስቀል፡ ተሸክሞ፡ የሚደገም።
ከላይ፡ ከሰማይ፡ ከግዜር፡ — ወደ፡ አዳም፡ ምድር፡
የተላከና፡ የሚላክ፡ — የመድኅኒያለም፡ መልክ፡
ትርጕሙኝ፡ ይላል፡ በየስልቱ፡ — ለሚደጋግሙቱ።
እኛም፡ ስንደግመው፡ መላልሰን፡ — ምሳሌ፡ እየሰጠን፡
እንፈታዋለን፡ በዋስ፡ — ድውይ፡ እንዲፈውስ።
ኮራ፡ ኮራ፡ እያልኸ፡ ካባ፡ ጋራ፡ — ስጥጣ፡ ስትርድ፡ ወደ፡ ኮራ፡
ብሉይ፡ ሐዲስ፡ ሊቅ፡ የምታማ፡ — አንተም፡ የዩም፡ ከተማ፡
ከትማልሙ፡ ጐንደር፡ — እንድትተባበር፡
ትቀምስ፡ እንደኾን፡ ትርጊሚ፡ — ጥዊት፡ ልስኘኸ፡ ለቅሚ።
ባይጣፍኘኽም፡ እንደ፡ ሰው፡ — ቀመስና፡ ተወው፤
ስንኳን፡ ኄቡኦ፡ ምስጢር፡ መና፡ — ማር፡ የማይኘመው፡ አለና።
በአዳም፡ ቍና፡ ባሕርይ፡ — የሴቶች፡ ዕዳ፡ ከፋይ፡
ዳግሚት፡ ሔዋን፡ ማርያም፡ — ልጇም፡ ዳግማይ፡ አዳም፡
ባሕታዊ፡ ልደት፡ መነኮስ፡ — ልደቱም፡ ብሉይ፡ ተሐዲስ፤
ገዳመ፡ ጾሙ፡ ድሩክ፡ — ቆቡም፡ አክሊለ፡ ሦክ፤
ቀናቱም፡ እሳት፡ አሚከላ፡ — ወገብ፡ የሚቈርጥ፡ የሚበላ፡
በቤተ፡ መቅደስ፡ በበአቱ፡ — ታኘቀት፡ ያዩት፡ አርድእቱ፤
ያዳምነቱም፡ አጫዋች፡ — ዩም፡ ወለድኩከ፡ ነች።
ካዲሳበባ፡ ከወንዙ፡ — ወደዲሳለም፡ ለሚጓዙ፡
ለሐዋርያት፡ ለማኀበሩ፡ — እስኪጠግቡና፡ እስኪሰክሩ፡
ቀምሶ፡ የሚያድል፡ የሚሰኘ፡ — ሰባት፡ ዐይነት፡ መጠኘ፡
ሊቀ፡ ረዳና፡ መጋቢው፡ — አበ፡ ማኀበሩም፡ ቃል፡ ሠግው፡
የአብርሃም፡ ዘር፡ የይሠሐቅ፡ — ሐዲስ፡ መልከ፡ ጼዴቅ።
እንደ፡ ኢያሱ፡ እንደ፡ ሙሴ፡ — ለማኀበረ፡ ሠላሴ፡
ተቀብቶ፡ ሲሾም፡ በሚገባ፡ — ዱራርቦ፡ ለብሷል፡ ቀሚስ፡ ካባ፡
ላንቃው፡ የእሳት፡ ነበልባል፡ — አርድእት፡ የሚያቃኘል።

www.ethiopianorthodox.org

ቀሚሱም፡ ያዳም፡ ልጅነት፡ — ካባውም፡ ክህነት፡ መንግሥት፤
ጸራርሮ፡ ሉብሶት፡ ስናየው፡ — አደማመቁ፡ ም፡ ሰው።
በትክሻው፡ ላይ፡ መኾኑ፡ — መስቀሉና፡ ሥልጣኑ፥
ኹሉም፡ ሠረ፡ ወኅ፡ ዐርበ፡ ወኅ፡ — ፍጹም፡ ሽልማት፡ ፍጹም፡ ጌጥ።
ዝሓ፡ በዝሓ፡ ሠራውን፡ — ቀርበው፡ ስላዩት፡ በዐይን፡
ሱራፌልና፡ ኪሩቤል፡ — አርድ፡ አንቀጥቅጥ፡ ይሉታል።
ከብሉይ፡ ኪዳን፡ ተለቅሞ፡ — በሐዲስ፡ ኪዳን፡ ታትሞ፡
ለዕብራውያን፡ ሲነበብ፡ — የሹመቱ፡ ክታብ፡
በቀራንዮ፡ በሎዛ፡ — ምስሌ፡ ጽንተ፡ ዱም፡ ይውሐዛ፡
ቀሚስ፡ ካባውን፡ አይቶ፡ ዳሶ፡ — ከበሽታው፡ ተፈውሶ፡
በዳጊመ፡ ቃል፡ መሳልሶ፡ — ማነው፡ የማይል፡ ዕሡ፡ ዕሡ፤
ወይም፡ ሐዊሳ፡ ሐዊሳ፡ — ለይሁዳዊው፡ አንበሳ፡
ከአዳም፡ ልጆች፡ ለሚበልጥ፡ — በመልክና፡ በጌጥ።
ስብሐት፡ ለአብም፡ ይ፡ ሸማኔ፡ — በመጠቅለያው፡ ቅኔ፡
ሲጠቀልለው፡ ልብሱን፡ ኹሉ፡ — እንዲህ፡ ይላል፡ በቃሉ፤
« እመኒ፡ ዘአልቦሙ፡ ልብ፡ ኢይሌብው፡ ዘ፡ ኵሎ፡
ልብ፡ ለዘቦቱ፡ ብሂለ፡ ተሠገወ፡ የአኩሎ » ።
የመልኩን፡ ውበት፡ ደም፡ ግባት፡ — ትኵር፡ ብሎ፡ ሲያዩት፡
ሐብረ፡ ምስሌው፡ ኪሩብማ፡ — ከፍጥረት፡ ኹሉ፡ የተስማማ፥
ያስማሙትም፡ ከፍጥረቱ፡ — ነፍስና፡ ሥጋው፡ ሰውነቱ።
ከእሑድ፡ ፍጥረት፡ መልአክ፡ — ልደት፡ የሚያበሥር፡ የሚሰብክ፥
የጥምቀቱንም፡ ነገር፡ — ተግቶ፡ የሚያስተምር።
ከሰኞም፡ ፍጥረት፡ ከማግሰኞ፡ — የቤተ፡ ክሲያን፡ መቃኞ፤
መዝጊያውም፡ የሮብ፡ ፩፡ ሳንቃ፡ — ፀሓዩና፡ ጨረቃ።
ከከዋክብቱም፡ ኮከብ፡ — ሰብአ፡ ሰገልን፡ የሚስብ፤
ኮከብነቱም፡ ብሩህ፡ — የያዕቆብ፡ ጽባሕ፡
በዝግ፡ ቤት፡ ገብቶ፡ ሲሠርቅ፡ — ባዙፍና፡ ረቂቅ።
ከኃሙስ፡ ፍጥረት፡ ባሕረ፡ ወኅ፡ — የጥምቀታችን፡ ጌጥ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩፻፲፰

ስሙም፡ ብጺሲ፡ ሐጼስ፡— የኒጳውሎስ፡ ልብስ።
ከዐርብም፡ ፍጥረት፡ ጥሩ፡ ዐይናማ፡— የኪሩቤል፡ ውሽማ፥
ዐይኑና፡ ቀንዱም፡ ሬዲላት፡— ኹሉም፡ ሰባት፡ ሰባት።
ምንም፡ ዐብረውት፡ ቢኖሩ፡— አይጠግብም፡ ፍቅሩ፤
ጽፍፍ፡ እያለው፡ ሐዋርያ፡— በአሕዛብ፡ ገበያ፡
ሰማዕታትን፡ እንደንጨት፡— የሚያቃጥል፡ እሳት።
ከአዳም፡ ልጆች፡ አዳም፡— ገጹ፡ ብጺሲ፡ ደም፡
ያዳም፡ የሔዋን፡ ደም፡ መላሽ፡— ሲዋጋና፡ ሲሸሽ።
ከአናብስቱም፡ ዲቦል፡— ግሩምና፡ ኀያል፡
ርሱ፡ ለሰይጣን፡ ሲያደባ፡— ከሰይጣን፡ ወጥመድ፡ የማይገባ።
ከላሞቹም፡ ላም፡ ጕሬዛ፡ ፌንዛ፡— በሠላሳ፡ ብር፡ የተገዛ፤
ወይም፡ ነጭ፡ ሎብ፡ ፍሪዳ፡— ከኰፉዎች፡ ጋር፡ የሚነዳ፡
በቀራንዮ፡ ሊታረድ፡— ፌርደውበት፡ አይሁድ።
ከንስሮቹም፡ ንስር፡ ሰራሪ፡— ፍጡርና፡ ፈጣሪ፡
ሰብስቦ፡ የሚያቅፍ፡ ልጆቹን፡— የተበተኑትን፤
የሞቱትንም፡ የሚያስነሣ፡— ትኩስና፡ ርጥብ፡ የርሱ፡ ሬሳ።
በደም፡ ሸማው፡ ላይ፡ በመስቀል፡— ክንፉን፡ ዘርግቶ፡ የሚሣል፤
የጥምቀትም፡ ለት፡ ሐለይት፡— የሰራ፡ ላይ፡ ወፍ፡ የሚሉት፥
አለርሱ፡ በቀር፡ ባለክንፍ፡— ማነው፡ የመስቀል፡ ወፍ፤
መስቀል፡ ጨቍኖት፡ በኛ፡ አበሳ፡— ሲወድቅና፡ ሲነሣ፡
ኹሉን፡ ወደ፡ ርሱ፡ የሚስብ፡— በመንፈሱ፡ ጥበብ።
ከባቦቹ፡ እባብ፡ አርዌ፡ ብርት፡— የነዝር፡ እባብ፡ መድኀኒት፡
እንደ፡ ባንዲራ፡ ተሰቅሎ፡— የሚፈውስ፡ በጥሎ፤
የመስቀሉም፡ ስም፡ ተራዳ፡— ለተያዙት፡ በፍዳ።
ከበጎቹም፡ በግ፡ የዋህ፡— ታስሮ፡ ሲሸለት፡ የማይጮኽ፤
በጲላጦስ፡ ፊት፡ በሸላቹ፡— ምንም፡ ቢሸሉ፡ ከንፈሮቹ፡
እንደ፡ በግ፡ እንጂ፡ እንደረኛ፡— አይናገርም፡ ኢጣሊኛ።
በረኛው፡ ቋንቋ፡ በቂሳር፡— በመንጋውም፡ ከንፈር፡

www.ethiopianorthodox.org

አለበትና፡ጸያፍ፡ቃል፡— ፖርኮ፡ዲዮ፡የሚል።

ማነው፡እንደ፡ሮም፡ታብዮ፡— እግዜርን፡የሚል፡ፖርኮ፡ዲዮ፡
ፖርኮው፡ሐሠማ፡ኽንዜር፡— ዲዮውም፡ሕያው፡እግዜር፡
የሕልም፡እንጀራ፡ምስጋናው፡— የማይጠገበው።
ስድቡም፡ሲሰማ፡ሲደመኝ፡— ጉሮሮ፡የሚያሳብኝ።

ከንጉሡ፡ታዘው፡ከጳጳሱ፡— ወታደሩና፡ቄሱ፡
እኾህ፡ዘሩባት፡በጦቢያው፡— ፖርኮ፡ዲዮ፡ብለው።

ኮቋቁር፡ቀሚስ፡የሚለብስ፡— ፋሽስት፡እንደ፡ጳጳስ፡
ስለ፡ምን፡ይኾን፡ብትለኝ፡— ኮሩ፡ማስረጃ፡አለኝ።
ገና፡ማየ፡አይኅ፡ሳይመጣ፡— ዲኖውም፡እግዜር፡ሳይቆጣ፡
ትንቢት፡ቀድሟታል፡ሮምን፡— በነሔኖክ፡ላሳን፤
በሔኖክ፡ትንቢት፡የሮም፡ጭፍራ፡— ተመሰሏል፡በቍራ፤
ቂሳራቸውም፡የሞት፡ኮሳ፡— በበግ፡ነጣቂው፡ተኵላ፥
እግዜር፡ሳይቆ፡ከሮም፡— በቋንቋና፡በዲም፡
እንዳያጠቃን፡ግራኝ፡— ሰላቅመን፡በቀኝ፡
የሮምን፡ተኵላ፡ትተን፡— ኦ፡እንከተል፡በጉን።

የበጎች፡አውራ፡ቃል፡ለሠጣው፡— በጲላጦስ፡ፊት፡የቆመው፡
ድምጡ፡የነብር፡ያንበሳ፡— ሲጮኽና፡ሲያገሣ፡
ከቁም፡ይኾላል፡የኋሊት፡— ተከታታይ፡ጠላት።

በቸር፡እረኛም፡ሲመሰል፡— ባለመቶ፡በግ፡ይባላል፤
እረኝነቱም፡በግ፡ወዳድ፡— ስለ፡ጠፋበት፡ከመቶ፡አንድ፡
ዘጠና፡ዘጠኝ፡እያሉት፡— ላንድ፡በግ፡ብሎ፡የሚሞት።

እኛንም፡በጎች፡ለማድረግ፡— ስለ፡ተሠዋ፡አንድ፡በግ፡
በትምራቱም፡ዕጹብ፡ድንቅ፡— ነዋ፡በግውን፡ለማጽደቅ፡
አለኑካቢ፡አላባት፡— ከማትመስለው፡እናት፡
የበግነቱ፡ምስክር፡— በግ፡ተወለደ፡ከጊደር፤
የበጉም፡ታሪክ፡የሚያጠጋብ፡— ዜና፡አይሁድን፡ለሚያነብ።

ፊሬርስ፡አቅራቢያ፡ሊተኰስ፡— ምሣዕና፡መቅደስ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፮

አይሁድም፡ወዲያው፡ሊከበቡ፡— እንደ፡ተሰበሰቡ፡
አመ፡ሰሙኑ፡ለኒሳን፡— ከዚያውም፡በነግህ፡ዐርብ፡ቀን፡
ቀርባ፡የነበር፡ልትሠዋ፡— እንስቲቱ፡ጣዕዋ፡
ተባት፡በግ፡ወልደ፡ስትልስ፡— ሕዝቡም፡ደንግጦ፡ሲላቀስ፡
ያን፡ጊዜ፡ዐሰሬቹ፡ቍሎ፡ብሳ፡— ኦሪት፡የወንጌል፡ጥላ።
በሰባ፡ሰባት፡ዓመት፡— ከኢየሱስ፡ልደት፡
ኢየሩሳሌም፡ስትጠፋ፡— ሙቶ፡ተቀብሯል፡ያይሁድ፡ተስፋ።
ቤተ፡አይሁድ፡ግን፡ቈማ፡ቀብሯ፡— አልተረዱትም፡ያርብን፡ሠራ፤
የቀዳሚንም፡በዓል፡— እንደ፡ሻረው፡ወንጌል።
አሑድ፡እንዲሾም፡በርሱ፡ፈንታ፡— ጌታ፡ሲሽረው፡ዐርብ፡ማታ፡
ተሰብኳልና፡ባለም፡ኹሉ፡— ቀዳም፡ሰዉር፡መባሉ።
ሰሳና፡ሰባ፡በሚኾን፡— በፈላሾች፡ዘመን፡
የጌዴዎን፡ልጅ፡ያች፡ጕሬዛ፡— ጕዲት፡ዐርባ፡ዓመት፡ስትገዛ፡
ምንም፡ቢበዙ፡ምልምሎቿ፡— ኹለት፡ናቸው፡ባሎቿ፤
ያገባቻቸው፡ባዋጅ፡— ወደ፡ቤተ፡ክሲያን፡ዲጅ።
፩ኛው፡ግዝረት፡ሰሞነኛ፡— የአብርሃም፡መልከኛ፤
፪ኛውም፡ቀዳም፡— የነዌሳው፡ወንድም፡
ለታናሹ፡እሑድ፡ለበለጠ፡— ብኵርናውን፡የሸጠ።
እጅ፡ሠራ፡ነው፡አኛንትማ፡— ቀዳም፡የእሑድ፡ዋዜማ፤
እሑድ፡ሰንበትም፡የሚብት፡— በሠረኛው፡ሰዓት።
ዐርብ፡ውሃ፡ቀድቶ፡እንጨት፡ሰብሮ፡— ቀዳሚንም፡አክብሮ፡
በ፳፡ቀን፡ተሸልቅቆ፡— ባ፵፡ቀንም፡ተጠምቆ፡
የጕዲትን፡ሕግ፡መጠበቅ፡— ታሪክ፡አለማወቅ።
ማነው፡የጕዲት፡እንደራሴ፡— አለጕዣም፡መነኵሴ፤
ጃን፡ደረባዋስ፡ማነው፡— አሳርብ፡ውሃ፡ቀጂው።
ዋሾቹ፡እንደኾን፡አባ፡ሆዴ፡— ፍትሐ፡ነገሥት፡ይታይ፤
ፍትሐ፡ነገሥቱም፡የተቀዳ፡— ከነጳውሎስ፡ጊዳ።
ነባቢው፡በግዕ፡ሠግው፡ቃል፡— ዐርብ፡ሲሠዋ፡ሲሰቀል፡

www.ethiopianorthodox.org

አይታ፡የማታይ፡ዐይናማ፡— ሰምታ፡የማትሰማ፡
የሹም፡ሸር፡ባሏን፡የምትከድ፡— ይችን፡ቤት፡አይሁድ፡
ሏምን፡እንበላት፡እንለስ፡— ይረቅ፡እንቡጥ፡የምትለስ፤
የፋሲካውን፡ጠቦት፡ቂጣ፡— ከምሳሌነት፡ሳታወጣ፡
እስካኹን፡ድረስ፡ገና፡አለች፡— ሐርሟን፡እንደ፡በላች።

በወንጌል፡ዕርሻ፡በዓለም፡— በነጳውሎስ፡ትልም፡
ከመንግሥተ፡ጽርእ፡በኋላ፡— በቅሎ፡ተወልዶ፡ዲቃላ፡
የአይሁድ፡ኹራት፡ወይም፡ቀንድ፡— ሐሳዌ፡መሲሕ፡ሙሐመድ፡
ምንም፡ቢቋዱስ፡ከናርድእቱ፡— በሰው፡ሠራሽ፡ትምርቱ፡
የቍርአን፡ትምርት፡ማየ፡አይኅ፡— እኛም፡ዱቂቀ፡ኖኅ፡
እንገሰዋለን፡በዐረብ፡— ይህን፡ዐሸን፡ከታብ።

ብሉይ፡ተሐዲስ፡ኪዳን፡— ነጫጭ፡ርግቦች፡አያሎን፤
ቍራን፡የቍራን፡መልክተኛ፡— ማነው፡የሚያምነው፡ከኛ፤
ላኢላ፡ሀኢላላ፡— አልመሲሕ፡ረሱል፡አላ፤
ኢላህ፡ወኢንሳን፡ተማም፡— አምላክና፡ሰው፡ፍጹም።

ላኢላም፡ማለት፡ሲተረክ፡— ሌላ፡አምላክ፡የለም፡አላምላክ፤
ካምላኮችንስ፡በቀር፡— ማነው፡አምላክ፡እግዜር።

ረሱል፡አላም፡ባማርኛ፡— መሲሕ፡የአምላክ፡መልክተኛ፤
ሰው፡ስለ፡ኾነ፡የግዜር፡ቃል፡— ረሱል፡አላ፡ይባላል።

የአብ፡ምሳሌ፡መሠረት፡— ከርሱ፡ለሚወጡት፤
ቃሉ፡መንፈሱ፡የአብ፡— ከባሕርዩ፡ከልብ፡
ሌላ፡አይባሉም፡በባሕርይ፡— ምንም፡አካል፡ስም፡ቢለያይ።

ከልብ፡ከቃል፡ከስትንፋስ፡— የማይለያይ፡የማይፈርስ፡
አንድነትና፡ሦስትነት፡— በቍርአን፡አለ፤ ተመልክት።

በግእዝና፡በአማርኛ፡— መጽሐፈ፡ቍርአን፡የት፡ሊገኝ፤
ዕጪ፡እንባቆም፡ከዐረብ፡— ወዳማርኛ፡ንባብ፡
ተርጕመውታል፡ይባላል፡— ባዒ፡ልብነ፡ድንግል፤
ዛሬም፡ይገኛል፡በዲማ፡— ለሚፈልገውማ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፻፷፪

ወዴ፡ግእዝም፡ካማርኛ፡— ዙራምቢ፡እንግዴ፡ኹለተኛ፡
የተረጐሙት፡ባኰስም፡— አሉ፡ይባላል፡ዛሬም።
አኵስም፡መኼዱም፡ቢሳንኽ፡— ሙፍቲን፡ተመልከት፡ፈልገኽ፤
ሙፍቲም፡የቍርአን፡ምዕላድ፡— ይመሰክራል፡ለወልድ።
ይሁዲና፡እስላም፡ኹለቱ፡— በኹለት፡ቋንቋ፡ሲሟገቱ፡
ወንጌል፡ሬታቹ፡ስለ፡ጽድቋ፡— በ፸፪፡ቋንቋ።
እውነት፡አንዲት፡ናት፡እንደግዜር፡— መቼ፡ዘጠኝ፡ዐሥር፤
ምርቷም፡ቢበዛ፡እንዴ፡ጊያ፡— አይጫንም፡ባህያ።
እውነትን፡በውነት፡ለሚሻት፡— ይበቃዋል፡ጥቂት፤
ለማርያ፡እኅት፡ለማርታ፡— እንዴ፡ነገራት፡ጌታ።
እውነት፡ለማይሻም፡በግእዙ፡— አይጠግበውም፡ብዙ።
ጥቂቱም፡ኾነ፡ብዙው፡— መሬት፡ካልተመቸው፡
ፍሬ፡አያፈራም፡በየክፍሉ፡— የተዘራው፡ቃል፡ኹሉ፤
ኋኑዪ፡ጌታችን፡ወልዴ፡ኋሬ፡— የወንጌሉ፡ገበሬ፡
ክፍሎታልና፡በስድስት፡— የዘራውን፡ቅንጣት።
እኩሉ፡በቅሎ፡የማይወልድ፡— እንዴ፡መካን፡እንዶድ፤
እኩሉ፡ባዝራ፡ወይም፡ላም፡— እጅግ፡ዘረ፡መልካም።
ከዘሩ፡አይዴለም፡ከቅንጣቱ፡— ማፍራት፡አለማፍራቱ፤
ከመሬት፡ብቻ፡ነው፡እንጂ፡— ያውም፡ባዴዘጋጅ፤
ዘሩስ፡መልካም፡ነው፡ሲዘራ፡— በማናቸውም፡ስፍራ፤
ምሳሌ፡ዘርዕም፡የሚያሳይ፡— የመሬቱን፡ጠባይ፡(ማቴ ፲፫፡፩–፳)።
የምኞት፡ጸሎትና፡ትንቢት፡— ስለ፡ሥልጣኔና፡ስለ፡ትምርት።
የመንግሥታችን፡ቀላድ፡ጣይ፡— አዴናይ፡አዴናይ፤
የኛንት፡ይብቃ፡አያልኽ፡በፍርድኽ፡— ስለ፡ዲኝነትኽ፡
አስፋ፡ወሰኗን፡በወሰን፡— ከግብጽ፡እስከ፡የመን።
ባሕረ፡ኤርትራን፡በመላው፡— ወገኗ፡ይጠጣው፤
ርሷም፡በመርከብ፡ትጋልብ፡— እንደናፂ፡ካሌብ፡
እየተመራች፡በዴመና፡— ወዴ፡መካ፡መዲና።

www.ethiopianorthodox.org

ዮርዳኖስንም፡ ተሻግራ፡ — ወደ፡ ጽዮን፡ ተራራ።
ደመናው፡ መንፈስ፡ ባለክንፍ፡ — የሚያቅፍ፡ የሚደግፍ፤
መሬጌታዋም፡ ቃል፡ ሥጋው፡ — መስቀል፡ የጨበጠው፤
አንገርጋሪውም፡ ቸር፡ አባቱ፡ — እስመ፡ ለዓለም፡ ምሕረቱ።
ዘቦ፡ እዝን፡ ሰሚዐ፡ ለይስማዕ፤ ወዘቦ፡ ልብ፡ ለብዎ፡ ለይለቡ።

በ፲፱፻፶፯፡ ዓ.ም፡ በሠኔ፡ ወር፡ አለቃ፡ ኪዳነ፡ ወልድ፡ ክፍሌ፡ ታመው፡ ሳሉ፡ ሊሞቱ፡ አቅራቢያ፡ ለደስታ፡ ተክለ፡ ወልድ፡ የነገሩት፡ ትንቢታዊ፡ ግጥም።

ያንበሳ፡ ደቦል፡ አንበሳ፡ ከግእዝ፡ አገር፡ ሲወጣ፡
መካ፡ መዲና፡ ትቀደስ፡ ኢየሩሳሌም፡ ትነጣ።
ከሰው፡ ጠማማ፡ ይታጣል፤ ከንጨትም፡ ደጋም፡ ጎባጣ።
የተዘጋውን፡ በትንቢት፡
ክፍቶ፡ ሲገባ፡ አየኹት።
ከሰዉ፡ ብዛት፡ ለጭፍራው፡
አኘዳኘድ፡ ደንጊያ፡ አይደርሰው።
ብመለከተው፡ የርሱ፡ ዐጀብ፡
ሃይማኖት፡ እውነት፡ ንቡብ።
ብመለከተው፡ የርሱን፡ አፉ፡
ሃይማኖት፡ ፍቅር፡ ወተስፋ።
ያንዲት፡ ላም፡ ወተት፡ አንድ፡ ዘሳ፡
ጌታዬ፡ ኢየሱስ፡ የገሊላ።
ክርሱ፡ ቢጎነጭ፡ ቢጥም፡ አዳሜ፡ ኹሉ፡ ሆዱ፡ ሞላ።
እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ለምኔ፡ ወደ፡ ገበያ፡ መውጣት፤
ለማየት፡ ነወይ፡ ለማየት፡
አዴፍ፡ በኘሩ፡ ሲሸመት።

www.ethiopianorthodox.org

| ማውጫ። | ገጽ፡ |
|---|---|
| ሃይማኖት፡ አበው፡ ቀደምት። | ፩ |
| ምክንያተ፡ ጽሒፍ፡ | ” |
| መዲና፡ ግኝም፡ ወይም፡ አጭሬ፡ | ፫ |
| የመጻሕፍት፡ ዐዋጅ፡ | ” |
| አርእስት፡ | ፯ |
| ጸሎት፡ | ” |
| አስረጅ፡ ዐማርኛ፡ . . . | ፲፩ |
| መቅድም። | ፲፯ |
| መዠመሪያ፡ ምዕራፍ። | |
| የጳጳሳትና፡ የባህላት፡ ታሪክ፡ | ፲፱ |
| ፪ኛ፡ ምዕራፍ። | |
| ስለ፡ ሠለስቱ፡ ባህላት፡ | ፳፫ |
| ክፍል፡ ቀዳማዊ፡ በእንተ፡ ተዋሕዶ፡ | ” |
| ሐተታ፡ | ” |
| የተዋሕዶ፡ ባህል፡ ንዋየ፡ ውስጥ፡ ... | ፳፯ |
| ክፍል፡ ካልእ፡ በእንተ፡ ቅብዐት፡ | ፴ |
| ክፍል፡ ሣልስ፡ በእንተ፡ መኖባሕት፡ | ፴፪ |
| ስፍጽ፤ ወይም፡ ዚቅ፡ | ፴፯ |
| ፫ኛ፡ ምዕራፍ። | ፵ |
| ፬ኛ፡ ምዕራፍ። | ፵፭ |
| ስፍጽ፡ እምዚና፡ ጐንደር፡ . . . | ፵፯ |
| ፭ኛ፡ ምዕራፍ። | ፶ |
| ፮ኛ፡ ምዕራፍ። | ፶፬ |
| ፯ኛ፡ ምዕራፍ። | ፶፰ |
| ፍትሐ፡ ነገሥት፡ . . . | ፶፱ |
| ፰ኛ፡ ምዕራፍ። | ፷፫ |

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| | ፪፻፸፭ |
| ፹ኛ፡ ምዕራፍ። | ፷፪ |
| አርእስተ፡ አዕማድ፡ ወምዕማድ፡ | ፸፩ |
| መዲና፡ ግኝም፡ የአዕማድ፡ መቅድም፡ | ፸፫ |
| ያሉቃ፡ ዕንቈ፡ ባሕርይ፡ ግኝም፡... | ፸፬ |
| አንቀጽ፡ ቀዳማዊ፡ በእንተ፡ ምስጢረ፡ ሥላሴ፡ | ፸፭ |
| መዝመሪያ፡ ክፍል። | 〃 |
| ፩ኛ፡ ክፍል። | ፸፯ |
| ፪ኛ፡ ክፍል። | ፸፱ |
| ፫ኛ፡ ክፍል። | ፹ |
| ፬ኛ፡ ክፍል። | ፹፪ |
| ፭ኛ፡ ክፍል። | ፹፰ |
| ፮ኛ፡ ክፍል። | ፺፪ |
| አንቀጽ፡ ካልእ፡ በእንተ፡ ምስጢረ፡ ሥጋዊ፡ | ፻፭ |
| ፩ኛ፡ ክፍል። | 〃 |
| ፪ኛ፡ ክፍል። | ፻፪ |
| ፫ኛ፡ ክፍል። | ፻፲ |
| ፬ኛ፡ ክፍል። | ፻፲፩ |
| ፭ኛ፡ ክፍል። | ፻፲፫ |
| ፮ኛ፡ ክፍል። | ፻፲፭ |
| ፯ኛ፡ ክፍል። | ፻፳፩ |
| ምስጢረ፡ ጥምቀት፡ | 〃 |
| ፰ኛ፡ ክፍል። | ፻፳፪ |
| ምስጢረ፡ ቍርባን፡ | 〃 |
| ፱ኛ፡ ክፍል። | ፻፳፫ |
| ምስጢረ፡ ትንሣኤ፡ | 〃 |
| ፲ኛ፡ ክፍል። | ፻፳፬ |
| ያሉቃ፡ ዕንቈ፡ ባሕርይ፡ ግኝም፡ ስላሠርቱና፡ ስለ፡ ስድስቱ፡ ቃላት። | ፻፳፰ |

www.ethiopianorthodox.org

፪፻፭፯

ስለ፡ ስድስቱ፡ ቃላት፡ ፻፭፱
ያሠርቱና፡ የስድስቱ፡ ቃላት፡ መርገፍና፡ አጫዋች፡
አርእስተ፡ መዝሙር፡ ሐዋዝ፡ ፻፷፱
ጸሎት፡ ወበውዳት፡ … ፻፷
፩ኛ፡ መትረብ። … ፻፷
ዋዜማ፡ ያንኮበር፡ ዐይናማ፡ ፻፷፪
ውዳሴ፡ ዕበዮን፡ ወክብሮን፡ ለሀብታተ፡ ክህነት፡
ወመንግሥት፡ ፻፷፮
፪ኛ፡ መትረብ። … ፻፷፱
ዕጣኑ፡ ሞገር፡ ዘአመ፡ ሰቡዑ፡ ለመስከረም፡ ፻፸፱
ስርዓ፤ አመጻሕፍተ፡ ሃይማኖት፡ አበው፡ ፻፸
፫ኛ፡ መትረብ፡ … ፻፸፪
የ፫ቱ፡ መትረቦች፡ መገናኛ፡ ግጥም፡ . . ፻፹፪
ክፍል፡ አሐዱ። ,, ፲
በእንተ፡ ቅዱስ፡ መጽሐፍ፡ ወበእንተ፡ ቅድስት፡ ሥላሴ፡ ,,
ክፍል፡ ካልእ። ፻፺
በእንተ፡ አሐዱ፡ አካል፡ ዐማኑኤል፡ ,,
ሥላሴ፡ ዘድንቅ፡ ማርቆስ፡ ኦርቶዶክሴ፡ ፻፺፰
ክፍል፡ ሣልስ። ,,
መወድስ፡ ዘኦርቶዶክሳዊ፡ ክፍለ፡ ዮሐንስ፡ ፻፺፪
ክፍል፡ ራብዕ።
በእንተ፡ ባሕርያት፡ ወግብራት፡ ወተዓቅቦቶን፡ —
እምሐውስታት፡ ፻፺፯
መወድስ፡ ዘዕዉር፡ ወልደ፡ ሃይማኖት፡ ኦርቶዶክሳዊ፡ ፪፻
ክፍል፡ ኃምስ። ,, ፭
በእንተ፡ ሣልስ፡ ልደት፡ ,, ,,
ክፍል፡ ሳድስ። ፪፻፰
በእንተ፡ ፅንሰ፡ ወፍሬ፡ ክርሣ፡ ለዮም፡ . . . ,,

www.ethiopianorthodox.org

፲፻፹፯

መወድስ፡ ዘአባ፡ ቋያ፡ መምህረ፡ አዘዘ፡ . . . ፲፻፺
ስሎጽ፡ ማእከለ፡ ሳድስ፡ ወሳብዕ፡ ክሌ፡ ፲፻፺
መወድስ፡ (ዘአለቃ፡ ተክለ፡ ጽዮን፡) 〃፺፫
ዐርኬ፡ 〃 ፬
እምኦርቶዶክሳዊ፡ ኪ፡ ወ፡ ክ፡ ዘልሳነ፡ ግእዝ፡ ላእክ፡ ፲፻፺፬
የታሪክ፡ ማስሮ፡ መጓሏሊት፡ ግጥም፡ 〃፺፭
እስመ፡ ለዓለም፡ ምሕረቱ፡ ፲፻ 〃

ክፍሌ፡ ሳብዕ፡ . . . 〃 ፯

የምኞት፡ ጸሎትና፡ ትንቢት፡ ስለ፡ ሠልጣኔና፡ —
ስለ፡ ትምርት፡ ፲፻፹፲

www.ethiopianorthodox.org

# STUDIEN ZUR KULTURKUNDE

Begründet von Leo Frobenius, herausgegeben von Eike Haberland

52 **Klaus E. Müller: Geschichte der antiken Ethnographie und ethnologischen Theoriebildung.** Von den Anfängen bis auf die byzantinischen Historiographen. Teil 2. 1980. (Teil I = Bd. 29 der Reihe). X, 563 S. m. 11 Abb., kart. DM 125,– ISBN 3-515-02499-9

53. **Asfa-Wossen Asserate: Die Geschichte von Šawā (Äthiopien) 1700–1865.** Nach dem tārika nagaśt von belāttēn gētā Ḫeruy Walda Śellāsē. 1980. XV, 165 S., kart. DM 28,– ISBN 3-515-02936-2

54 **A. B. C. Ocholla-Ayayo: The Luo Culture.** A Reconstruction of the Material Culture Patterns of a Traditional African Society. 1980. XV, 210 S. m. 75 Abb., kart. DM 39,– ISBN 3-515-02925-7

55 **Andreas Massing: The Economic Anthropology of the Kru (West Africa).** 1980. XII, 281 S. m. 43 Fig. u. 19 Ktn., kart. DM 48,– ISBN 3-515-03162-6

56 **Gordon D. Gibson, Thomas J. Larson, Cecilia R. McGurk: The Kavango Peoples.** 1981. VIII, 276 S., 15 Taf. m. 27 Abb., kart. DM 48,– ISBN 3-515-03343-2

57 **Barbara Frank: Die Kulere – Bauern in Mittelnigeria.** 1981. XIII, 267 S., 56 Taf., kart. DM 75,– ISBN 3-515-03268-1

58 **Waltraud und Andreas Kronenberg: Die Bongo.** Bauern und Jäger im Südsudan. 1981. XIV, 357 S. m. 150 Abb. u. 34 Taf., kart. DM 74,– ISBN 3-515-03301-7

59 **Christoph Staewen/Friderun Schönberg: Ifa, das Wort der Götter.** Orakeltexte der Yoruba in Nigeria. 1981. XIV, 235 S., kart. DM 44,– ISBN 3-515-3604-0

60a **Christraud Geary: Things of the Palace:** A Catalogue of the Bamum Palace Museum in Foumban (Cameroun). 1983. XVI, 279 S. m. 153 Abb. u. 24 Fotos, 80 Taf. m. 124 Fotos, kart. DM 72,– (engl. Ausgabe) ISBN 3-515-02924-9

60b **–: „Les choses du palais":** Catalogue du Musée du Palais Bamoum à Foumban (Cameroun). 1984. XVI, 299 S. m. 24 Fotos, 153 Abb. u. 2 Ktn., 80 Taf. m. 124 Fotos, kt. DM 72,– (französ. Ausgabe) ISBN 3-515-03793-4

61 **Werner J. Lange: History of the Southern Gonga.** 1982. XVIII, 348 S. m. 15 Abb., 12 Taf., 7 Ktn., kart. DM 78,– ISBN 3-515-03399-8

62 **Y. Georges Madiéga: Contribution à l'histoire précoloniale du Gulma (Haute-Volta).** 1982. XII, 260 S. m. 11 Ktn., kart. DM 58,– ISBN 3-515-03222-3

63 **Wolf Leslau: Gurage Folklore.** Ethiopian Folktales, Proverbs, Beliefs, and Riddles. 1982. XIV, 327 S., kart. DM 118,– ISBN 3-515-03513-3

64 **Karl Heinz Striedter: Felsbilder Nordafrikas und der Sahara.** Ein Verfahren zu ihrer systematischen Erfassung und Auswertung. 1983. VIII, 287 S. m. 19 Abb., kt. DM 58,– ISBN 3-515-03397-1

65 **Ulrich Braukämper: Die Kambata.** Geschichte und Gesellschaft eines südäthiopischen Bauernvolkes. 1983. XIV, 330 S., 9 Taf. u. 7 Ktn., kt. DM 82,– ISBN 3-515-03747-0

66 **Adam Jones: German Sources for West African History, 1599–1669.** 1983. XII, 406 S., kt. DM 76,– ISBN 3-515-03728-4

67 **Peter Fuchs: Das Brot der Wüste.** Sozio-Ökonomie der Sahara-Kanuri von Fachi. 1983. XIV, 240 S. m. 26 Abb., 16 Taf. u. 8 Fotos, kt. DM 69,– ISBN 3-515-03764-0

68 **Adam Jones: From Slaves to Palm Kernels.** A History of the Galinhas Country (West Africa), 1730–1890. 1983. XVIII, 220 S. m. 29 Abb., 13 Taf., kt. DM 48,– ISBN 3-515-03878-7

69 **Roland Mischung: Religion und Wirklichkeitsvorstellungen in einem Karen-Dorf Nordwest-Thailands.** 1984. XIII, 362 S. m. 24 Abb., 4 Ktn. u. 12 Taf., kt. DM 74,– ISBN 3-515-03227-4

70 **Leo Frobenius: Mythes et contes populaires des riverains du Kasaï.** Traduction de l'allemand par Claude Murat. 1983. XII, 326 S., kt. DM 74,– ISBN 3-515-03922-8

71 **Samson O. O. Amali: An Ancient Nigerian Drama.** The Idoma Inquest. A bilingual presentation in Idoma and English together with ODEGWUDEGWU an original bilingual play in Idoma and English. 1985. VII, 241 S., kt. DM 48,– ISBN 3-515-04097-8

72 **Anne-Marie Duperray: Les Gourounsi de Haute-Volta.** Conquête et colonisation 1896–1933. 1984. XIV, 280 S. m. 26 Ktn., kt. DM 58,– ISBN 3-515-04112-5

73 **Steven Kaplan: The Monastic Holy Man and the Christianization of Early Solomonic Ethiopia.** 1984. XIV, 150 S. m. 1 Skizze, kt. DM 36,– ISBN 3-515-03934-1

74 **Renate Wente-Lukas: Handbook of Ethnic Units in Nigeria.** With the Assistance of Adam Jones. 1985. VIII, 466 S., kt. DM 112,– ISBN 3-515-03624-5

75 **Beatrix Heintze: Fontes para a história de Angola do século XVII.** I. Memórias, relações e outros manuscritos da Colectânea Documental de Fernão de Sousa (1622–1635). 1985. XV, 419 S. m. 11 Abb. u. 14 Fotos, kt. DM 98,– ISBN 3-515-04260-1

76 **Jean-Pierre Warnier: Echanges, développement et hiérarchies dans le Bamenda précolonial (Cameroun).** 1985. XIV, 323 S. m. 16 Ktn. u. 14 Abb., kt. DM 60,– ISBN 3-515-04281-4

*Fortsetzung siehe nächste Seite*

www.ethiopianorthodox.org

